# ትንሣኤ




ቁጥር ፳፩

[redacted] ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ፡፡ »

አዘጋጅ
ራደ አስረስ ፣


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
ኢየታተመ የሚወጣ ፡፡

የፖስት ሣጥን ቁጥር 1068
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፣


# ማ ው ጫ

## አርእስት ፣ ገጽ


ድብዳቤዎች . . . . . . . . . . . . . . . ፩
የሕፃኑ ኢየሱስ በረከት በአፍሪቃ ምድር . . . . . ፪
ተወዳጁ ሐኪም ቅዱስ ሉቃስ . . . . . . . . ፬
እምሙ ለሰማዕት (የሰማዕታት እናታቸው) . . . . . ፯
ቅዱስ ማቴዎስ . . . . . . . . . . . . . ፰
ወጣቶች በመስቀልና በወርኃ ጽጌ . . . . . . . ፲
የጽጌ ማኅሌትና የጽጌ ጾም መቼ ተጀመረ ! . . . . ፲፩
ቅዱስ ጋብቻ . . . . . . . . . . . . . ፲፫
የመጀመሪያው መርከብ ሠሪ . . . . . . . . ፲፬
የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ . . . . . ፲፭
ዜና ሊቃውንት . . . . . . . . . . . . ፲፯
ሥርዓተ ገዳም . . . . . . . . . . . . ፲፰
በሕፃናት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ በሽታዎች . . . . . ፳
ትምህርተ ግዕዝ . . . . . . . . . . . . ፳፬


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በመስቀል ላይ ከቆየ በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ወይቤ ተፈጸመ ኵሉ » ሁሉ ተፈጸመ » በማለት ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው ለይቶ መለኮት በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ሲወርድ በአካለ ነፍስ ደግሞ ወደሲኦል ወርዶ በግዞት የነበሩ ነፍሳትን ከማዕሠረ ኃጢአት ፈትቶ ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ እንዳወጣቸው የታወቀ ነው ፡፡ በዚህም መሠረት በየዓመቱ የስቅለት ዕለት ከአሥራ አንድ ሰዓት በኋላ ኑዛዜና እግዚአብሔር ይፍታሕ ማለት ይገባል ብለን ስናስተምር አንዳንድ ሰዎች «ወተንሥአ እግዚአብሔር » ካልተባለ ማለት የትንሣኤው የምሥራች ካልተነገረ «እግዚአብሔር ይፍታሕ » ሊባል አይገባም ይላሉ ትክክለኛው የቱ ነው ?

፪- የቀዳም ስዑር የአክፍሎት ጾም ሲሆን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለምን ይቀደሳል ? ምእመናኑ ጸዋሚዎች ከሆኑ ሥጋውንና ደሙን ማን ሊቀበለው ይቀደሳል ?

፫ኛ- ቅዱስ ጳውሎስ ወደዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ምዕራፍ ሰባት ቁጥር ፫ ላይ ስለመልከ ጼዴቅ «አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም » የሚለው ኃይለ ቃል ለአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ስለሚያስቸግር የመልከጼዴቅ ትውልድ ከማን ነገድ እንደሆነና ሐዋርያውም ከላይ የተጠቀሰውን ኃይለ ቃል ስለምን እንደጻፈ ይብራራልኝ ፡፡

**መምህር ሲሳይ አካሉ**
የሰላሌ አውራጃ የወንጌል መልእክተኛ

**መምህር ስለ ጥያቄዎ እናመሰግና**ለን የወንጌል መልእክት ሥራዎም በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የተሳካ ይሆን ዘንድ እንመኛለን አንዳንድ ሊቃውንት በየዓመቱ በዓለ ስቅለትን በምናከብርበት ጊዜ በሠርክ ማለት ከዘጠኝ ሰዓት ሥዕለ ሥቅለት ከወረደና «ንሴብሖ » ከበተባለ በኋላ ኑዛዜ ናዝዞ « እግዚአብሔር ይፍታሕ » ማለት አይገባም ሲሉ አንዳንዶቹ ሲያስረዱ ግን እግዚአብሔር ይፍታሕ ይባላል ይሉና ነፍሳት ከግብርናተ ዲያብሎስ ተላቅቀው ፡፡ ከማዕሠረ ኃጢአት ተፈትተዋልና በማለት ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አስተምረዋል ፡፡ ዛሬም ያስተምራሉ ፡፡ እኛም ከቀደሙትና አሁንም ካሉት እንደተማርነው በየዓመቱ የሕማማትን ሳምንት በጾምና በጸሎት በምህላና በስግደት ብቻ ስናከብር እንደቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት ለሕያዋንም ሥርዓተ ኑዛዜ አይደረግም፣ ከዓርብ ሠርክ (ዘጠኝ ሰዓት ) ንሴብሖ ከተባለ በኋላ ግን ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት ለሕያዋንም ሥርዓተ ኑዛዜ ማድረስና እግዚአብሔር ይፍታሕ ማለትም ይገባል ይላሉ ትክክለኛውም ይህ ይመስላል ፡፡

ስለ ፪ኛው ጥያቄ ግን ብፁዕ አቡነ በርናባስን አነጋግረን ነበር እርሳቸውም የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል የቅዳም ስዑር እርግጥ ጾም ነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም በጾም ቀናት ከሰዓት በፊት ቅዳሴ ክልክል ነው የቅዳም ሥዑር ጾምም ሰዓት የሚደረሰው ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ በመንፈቀ ሌሊት ስለሆነ ከዚያ በፊት ቅዳሴ ሊቀደስ አይገባም በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፱-፯፻፳፪ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስከብ በመቃብር ከሆነባት ዕለተ ሰንበት ( ቅዳም ስዑር) በቀር በቀሩት ሰንበታትና እሁዳት በየሳምንቱ ሥርዓተ ቁርባንን መፈጸም እንደሚገባ ተገልጦ ተወስኖአል፡፡ በዚህም መሠረት በታላላቁ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት የቅዳም ስዑር ዕለት አይቀደስም መቀደስ እንደሌለበትም ትምህርት በሰፊው ይሰጣል ፡፡

ምን አልባት ይቀደሳል የሚሉ ክፍሎች ቅዱስ ያሬድ ዕጣነ ሞገር ስለሠራ ነው ይሉ ይሆናል ፤ ዕርግጥ ነው ቅዱስ ያሬድ ለዓርብ ዕለትም ሠርቶአል ለቅዳሜ ብቻ አይደለም ፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክንያት የቅዳም ስዑር ዕለት ቅዳሴ እንደማይገባ ከመምህሮቼ የተማርኩትና የኔም እምነት ነው በማለት ገልጠዋል ፡፡

በተጨማሪም ስለዚሁ ጥያቄ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ መጋቤ ካህናት ብርሃኑ መኮንንን አነጋግረናል እርሳቸውም « በዜማ ባሕል የሐሙስና የዓርብ ጸሎተ አኰቴት ለሰኞ ለማክሰኞና ለረቡዕም የተመደበ ስለሆነ የቅዳሜ ሥዑር ዕለት ቅዳሴ ሊኖር አይገባም ቅዱስ ያሬድም ለዓርብም ሆነ ለቅዳሜ ሥዑር ዕጣነ ሞገር ቢሠራም አብዛኛዎቹ ሊቃውንት የሚስማሙ በጾምነቱ ነው » በማለት ተመሳሳይ መልስ ሰጥተውናል ፡፡

፫ኛ በዕብራውያን መልእክት ፯-፫ ላይ እንደተገለጠው « መልከ ጼዴቅ» አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም - - - » የተባሉትን ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚከተለው ያትታሉ ፡፡ እንደ አይሁድ ትውፊት መልከ ጼዴቅ ከማየ አይህ የተረፈውና በምድር ላይ ለረዥም ዘመን የኖረ የኖኅ ልጅ ሴም እንደሆነ ይናገራሉ ፡፡ እንደ እነ ሄኖክ ም እስከ አሁን በሕይወት አለ ይላሉ ፡፡ እንዲሁም ከማየ አይህ በኋላ ለነበሩ አባቶች ( ፓትሪያርኮች ) መልከ ጼዴቅ ካህን

( ወደ፲፯ኛው ገጽ ዞሯል )

www.ethiopianorthodox.org

( ርእሰ አንቀጽ )

# የሕፃኑ ኢየሱስ በረከት በአፍሪቃ ምድር

«የምድር አሕዛብ ሁሉ (በዘርህ) በክርስቶስ የተባረኩ ይሆናሉ» ተብሎ ለአብርሃም የተነገረለት የተስፋ ቃል፣ ለአፍሪቃም መትረፉን የሕፃኑ ኢየሱስ ወደግብፅ መሰደድና በሰላም መመለስ ያስረዳናል። ዳዊትም በመዝሙሩ «ለነርሱ የቃል ኪዳን ምልክት የሆነውን ቃል ሰጣቸው» ካለ በኋላ፤ «ወመንክሮሂ በምድረ ካም» ድንቅ ሥራውንም በካም ምድር አደረገ በማለት የተናገረው ትንቢት በዚሁ ስለመፈጸሙ አንጠራጠርም።

ነቢዩ ኢሳይያስም «ወይወርድ እግዚእነ ውስተ ምድረ ግብፅ እንዘ ይጼዓን ዲበ ደመና ቀሊል» እነሆ ጌታችን በደመና ሆኖ ማለትም በዘባነ እሙ ወደግብፅ ይወርዳል በማለት ትንቢት ተናግሮ እንደነበር ይታወሳል። ይህም የሆነበት ምክንያተ ነገር፣ ምድረ ግብፅ ከታላቁ እስክንድር ግብታዊ ሞት በኋላ ፕቶለሚ በሚል ስም ለሚጠራው የጦር አበጋዝ ድርሻ ሆና በመሰጠትዋ በእስክንድር እስከንድርያ አሰኝቶ ዘርዓ መንግሥት መሥርቶ ይኖር ከነበረበት ጊዜ አንሥቶ ብዙ አይሁድ እየተሰደዱ በዚያች አገር ይኖሩ ነበር። ስለዚህም ኦኒያስ ወልደ ስምዖን የተሰኘ አንድ አይሁዳዊ ካህን ከአንጾኪያ ተሰዶ ወደግብፅ በመውረዱ ቀድሞ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም አሠርቶት የነበረውን የሚመስል ቤተ መቅደስ ሠርቶ ነበር። ለዚህም መሠረት የሆነው «እንዲት አገር ምድረ ግብፅ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረቢያ ትሆናለች፤ በዚያም ዘመን እግዚአብሔር በግብፅ ምድር የታወቀ ይሆናል፤ እርሱም መድኃኒትን ሰዶ (ልኮ) ያድናቸዋል» ተብሎ የተነገረው ትንቢት ነው። (ኢሳ ፲፱፣ ፲፱—፳፩)

መድኃኒት ተብሎም የተጠራው ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰባ ሊቃናት እሥራኤል ተመርጠው የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍ ከዕብራይስጥ ወደጽርዕ (ግሪክኛ) የተረጎሙትም በዚህችው በእስክንድርያ ከተማ ነበር። ስለዚህም ይህን በመሳሰለው ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ትንቢትና የተስፋው ተካፋይ የሆነች አፍሪቃችን በተለይም እስክንድርያ እስከ ምጽአተ ክርስቶስ «ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ». በሚለው እምነት ጸንተው ለሚኖሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መፍለቂያ መዲና ሆና በዓለም ታሪክ ለመመዝገብ በቅታለች።

ታዲያ ይህ በረከት በግብፅ ብቻ ተወስኖ አልቀረም፤ በይበልጥም ለኢትዮጵያችን የተሰጠው በከፊል ሳይሆን በምልዓት ነው። ለማስረጃም ያህል፣ ቅዱስ መጽሐፍ ኢትዮጵያን ከ፴ ጊዜ ይበልጥ ይጠራታል። ከዚህም ውስጥ «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሎ በነቢዩ ዳዊት መዝሙር ፷፰ የተጻፈው፤ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከጥንት ጀምሮ ከእግዚአብሔር ዘንድ የነበራቸውን ጸጋና በረከት የሚገልጥ ነው። በዚሁ ሳቢያ አሁንም መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በሕፃንነቱ ወደግብፅ ምድር በወረደ ጊዜ አልፎ ወደኢትዮጵያ በመምጣት ምድራችንን የባረካት መሆኑን የሚያስረዳ ታሪክ አለን። እንዲያውም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሕፃኑ ጌታ ኢየሱስ ጋር የተሻለ ዕረፍትና የተሻለም አቀባበል ያገኘችው ከግብፅ ይበልጥ በኢትዮጵያ መሆኑ ይነገራል። ካረፈችባቸውም ቦታዎች ዋናው ጣና ሐይቅ ውስጥ ዛሬ የኪዳነ ምሕረት ገዳም እየተባለ የሚጠራው ክፍል ነው ተብሏል።

ሌላም በረከት አለ። ይኸውም ኢትዮጵያና ሕዝብዋ ለእመቤታችን የቃል ኪዳን ምድርና የቃል ኪዳን ልጆች ሆነው መሰጠታቸው ነው። እመቤታችን በዚህ ዓለም ለደረሰባት ስደትና ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራ ሁሉ መጽናኛ እንዲሆናት ጌታ ከሰጣት ታላላቅ የተስፋ ቃል ኪዳኖች አንዱ አማላጅነትዋን አምነው ለሚቀበሉ ሁሉ የቃል ኪዳን እናት እንድትሆን ማድረጉ ነው። አሁንም ይህ



ቃል ኪዳን በሥራ ላይ ነው።

ታዲያ የቃል ኪዳን ልጅነታችን መታወቂያ ምልክት ምንድን ነው? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት እመቤታችን ከቃል ኪዳን ልጆችዋ የምትፈልገውን ቁም ነገር ማወቅ ያስፈልጋል። ይኸውም እርስዋ ከጌታ ልደት እስከ እግረ መስቀሉ በተጓዘችበት ጊዜ ሁሉ ያን ሁሉ ፀዋትወ መከራ ሳትሰቀቅ ጸንታ እንደቆመች፤ እኛም የቃል ኪዳን ልጆችዋ የርስዋን አርአያነትና ምሳሌነት በመከተል እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ድረስ እንኳ ቢሆን በውድ ልጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነትና ፍቅር ጸንተን እንድንገኝ ይፈለግብናል። ነገር ግን የወንጌሉን ቃል ሰምተን ትእዛዙን ተምረን የርሱን አዳኝነት ሳናምን ሆዴ ይሙላ፤ ደረቴ ይቅላ በማለት ዘመናችንን በንዝኅላልነት ፈጽመን በዚያ የመጨረሻ ፍርድ ቀን ያማላጅ ያለህ ማለቱ የሚያዋጣ አለመሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። የእመቤታችን ቃል ኪዳን እናትነትና አማላጅነትም የሚሠራው ለአማኞች እንጂ ለኢአማንያን አይደለምና።

ስለዚህም «ስደተ ሕፃን አጉየየ ለሰይጣን፤» የሕፃኑ ኢየሱስ ስደት ሰይጣንን ከምዕመናን ልብ እንዲሰደድ አድርጎታል ተብሎ እንደተጻፈ፣ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ምቀኝነትንና በጠቅላላ የኃጢአትን ሥራ ሁሉ የሚያሳስብ ፀረ ሰላም፣ ፀረ—ፍቅር፣ ፀረ—አንድነት የሆነውን የሰይጣንን ኃይል ሰብሮ ለስደተኞች መጠጊያ ምዕራፍ፣ በባሕር ለሚጓዙም ሁሉ መርከብ የሆነ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ ወደሀገራችን በመሰደድ የሰጠንን ጸጋና በረከት ሁሉ ለመቀበል በስሙ አምኖ፣ በሕጉ ጸንቶ መገኘት ያስፈልጋል።



www.ethiopianorthodox.org

# « ተወዳጁ ሐኪም ቅዱስ ሉቃስ »

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይከተሉት የነበሩት ሰዎች ከተለያየ ብሔረ ሰብ እ የመጡ ልዩ ልዩ ሃይማኖትና ባህል ያላቸው ነበሩ ። ድሆች ብቻ ሳይሆኑ ባለጠጐችም ያላቸውን ንብረት ሁሉ በመተው ተከትለውታል ። ተከታዮቹ ያልተማሩት ብቻ አልነበሩም ። ከፍተኛ ትምህርትና ሙያ ችሎታ የነበራቸውም አምነው የእርሱ ተከታዮች ሆነዋል ።

ሕግ ዐዋቂዎች እንደ እንኒቆዲሞስና እንደዮሴፍ ዘአርማትያስ ፤ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው እንደ መቶ አለቃውና እንደ መኰንኑ እያኢሮስ ያሉት ሁሉ ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው አምላክነቱን በመረዳት አምነው ተከታዮቹ እንደ ሆኑ ወንጌል ያስረዳል (ማቴ ፰፥ ፭ ። ማር ፭ ፥ ፳፪—፳፬) ።

ከተከታዮቹ መካከል ከፍተኛ ዕውቀት እንደነበረው የተመሰከረለት ቅዱስ ሉቃስ ነው ። ሉቃስ በአንፆኪያ ተወለደ ። ይሁን እንጂ ትውልዱ ግሪክ ነው ። ከ፲፪ ሐዋርያትም ጋር እንደ ተጠራ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አልተጠቀሰም ። ነገር ግን ቍጥሩ ከሰባ ሁለት አርድእት (ከሰባው ደቀ መዛሙርት) መሆኑ በሊቃውንት ታምኖአል። (ሉቃ ፤ ፲ ፤ ፩) ። በሉቃስ ወንጌል ፳፬ ፤ ፲፫—፴፭ ላይ ከቀለዮጳ ጋር ወደ ኤማሁስ ይሄድ የነበረው ጌታን ከሙታን ከተነሣ በኋላ ያየውና ያነጋገረውን ደቀ መዝሙር ቅዱስ ሉቃስ እንደሆነ የአዲስ ኪዳን ሊቃውንት ይተረጉማሉ ።

በዚህ መሠረት ቅዱስ ሉቃስ ጌታን አይቶአል ። ከጌታ ተምሮአል ተአምራቱንም ተመልክቶአል ። ባየው በሰማው ሁሉ ምስክር ለመሆን በቅቶአል ።

ትውፊት እንደሚያስረዳ ሉቃስ ከአራቱ ወንጌሎች ሦስተኛውን በስሙ የሚጠራውን ወንጌል ጽፎአል ። የሐዋርያት ሥራንም የጻፈ እርሱ ነው ። ሁለቱንም በግሪክ ቋንቋ ጽፎአቸዋል ። የጻፋቸውም ቴዎፍሎስ ለተባለ ለመቄዶንያው (ግሪክ ) ባለ ሥልጣን ነው ። አይሁዳዊ ያልሆነ ከአሕዛብ ወገን የመጀመሪያው የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊ ሉቃስ ብቻ ስለሆነ አይሁድ ያልሆኑ ሁሉ እጅግ ይኰሩበታል ።

በሉቃስ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ ያለው የታሪክ አቀራረብ ትክክለኛ እንደሆነ በመጀመሪያውና በመካከለኛው የክርስትና ዘመን የነበሩ ሊቃውንት ሁሉ አምነውበታል ። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ሉቃስ ከሌሎች ወንጌላውያን ይልቅ ተራቀናል ይላሉ ። በዚህም የምዕራብ አውሮጳ ክርስቲያኖች በጣም ይመኩበታል ።

ሉቃስ የቅዱስ ጳውሎስ የወንጌል ሥራ ጓደኛ ነበር ። በተለይም በሁለተኛውና በሦስተኛው የስብከት ጉዞው ከቅዱስ ጳውሎስ አልተለየም ነበር ። ፪ጢሞ ፬ ፥ ፲፩ ። ፊል ፪ ፤ ፬) ። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውንም ታሪክ የሰበሰበ በዚህ ጊዜ ነው ። ከጳውሎስ ። ጋር የሥራ ተባባሪ መሆኑን «እኛ» በማለት ራሱን ከጳውሎስና ከሌሎች የወንጌል ሰባኪዎች ጋር ጨምሮ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ገልጦአል ። (የሐዋ ፲፮ ፥፲፪ ። ፳ ፥ ፭—፯)

በ፪ኛ ቆሮንቶስ ፰ ፤ ፲፰ እንደዚሁም ፲፪ ፥ ፲፰ ላይ «ከእርሱም (ከቲቶ) ጋር ስለ ወንጌል ስብከት በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን ወንድም እንልካለን» ቲቶን መከርሁት ከእርሱም ጋር ወንድሙን ላክሁት የሚሉትን ዓረፍተ ነገሮች በመመርመር ሉቃስ የቲቶ ወንድም እንደሆነ ኦሪጅኖስና አውሳብዮስ ጽፈዋል ። ሄሮኒሞስም በዚህ ሐሳብ ተስማምቶአል ።

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ሉቅዮስ ወይም ሉክዮስ በመባል የሚጠራ ሌላ ሰው እንደ ነበር በሐዋርያት ሥራ፲፫ ፥ ፩ እና በሮሜ ፲፮ ፥ ፳፩ ላይ ተጠቅሶአል። ይህንም ይዘው «ሉቅዮስ የተባለ ሉቃስ ነው ያሉ ሊቃውንት አሉ ። ምክንቱም የስሙ አጠራር በተለያዩ ቋንቋዎች የተለያዩ አጠራር ስላለው ነው ለምሳሌ በግሪክ ሉቃስ ፤ በእንግሉሳክሶን ሉክዮስ በላቲን ሉቅዮስ ይባላልና ። በዚህም መነሻነት ሉቃስ አይሁዳዊ እንደሆነ የተናገሩና የጻፉ ሊቃውንተ አይሁድ አሉ ። ምክንያቱም አይሁዳዊው ጳውሎስ ዘመዴ ሉቅዮስ ይለዋልና (ሮሜ ፲፮ ፥ ፳፩) ። ይሁን እንጂ ይህ አስተያየት በብዙዎች ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት ያለው መስሎ አይታይም ።

ቅዱስ ሉቃስ የሕክምና ዶክተር ነበር ይህ ሥራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እጅግ ተወዳጅነትን አትርፎለታል (ቆላ፬—፲፬ ። ሐኪም መሆኑ በማንኛውም ኅብረተሰብ መካከል ወንጌልን ለማስተማር መግቢያ በር በመሆን ጠቅሞታል ። የሕዝቡን ደዌ ነፍሳቸውን በትምህርት ሲፈውስ ደዌ ሥጋቸውን ደግሞ በሕክምና ለመፈወስ ይችላልና ። ቅዱስ ሉቃስ የሕክምና ሙያውን ያጠናው ከአቴናና ከእስክንድርያ ሊቃውንት እንደሆነ ይነገራል ። በዚያ ዘመን በሁሉም ዕውቀት የሰለጠኑ እነዚህ ሁለቱ ከተሞች ነበሩና ። ሉቃስ የሕክምና ችሎታ እንደነበረው ስለደጉ ሳምራዊና በወንበዴዎች ስለቆሰለው መንገደኛ በጻፈው ምሳሌ በግልጥ መረዳት ይቻላል (ሉቃ ፲ ፥ ፴ —፴፯) ከሐዋርያትና ከሰባ አርድእት መካከል የሕክምና ባለሙያ የነበረ አሕዛባዊው ሉቃስ በመሆኑ በግሪኮች



ዘንድ እጅግ ተወዳጅነት አለው ።

ከዚህም ሌላ ቅዱስ ሉቃስ ሥዕል ሠዓሊ ነበር ። ሠዓሊነቱ በቀለም። በቅርጽ ብቻ ሳይሆን በቃላትም ነው። ይህም የሥእላዊ ታሪክ አቀራረብ ችሎታውን ይገልጣል ። ለምሳሌ ስለ ጠፋው ልጅና ስለ ደጉ ሳምራዊ የጻፈው ምሳሌ የሥዕላዊ ታሪክ አቀራረብ ነውና ።

ቅዱስ ሉቃስ እንደሳላቸው የሚነገርላቸው የእመቤታችን ሥዕሎች በኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እስካሁን ድረስ አሉ



ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ክርስቶስ በላሞች በረት መወለዱን ሲጽፍ ፤

በኢትዮጵያ ውስጥ በተድባበ ማርያም በደብረ ዘመዶ (ወሎ ፤ በደብረ ወርቅ በዋሸራ በጅበላ (ጎጃም) በአውሮፓ ውስጥ በእስፓንያ በቅድስት ማርያም ካቴድራል ሉቃስ ሣላቸው የሚባሉት የእመቤታችን ሥዕሎች ይገኛሉ ። እነዚህም ሥዕሎች በኢትዮጵያ የተለየ ስም አላቸው ። «መንክር ኃይላ ወይኒቱ እሆ በሃሊትን» ይባላሉ ። አንዳንድ ጊዜም ከእነዚህ ሥዕሎች ልዩ ምልክት እንደሚታይ ይነገራል ።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የሉቃስን ሠዓሊነት ሲገልጡ «እመቤታችን ሆይ ከወንጌላውያን አንዱ ዶክተር ሉቃስ በእጁ ለሣላት ሥዕል ሰላምታ ይገባል» ብለዋል ። ነገር ግን አንዳንድ ዘመናውያን ሊቃውንት ሥዕሎችን መርምረው ባገኙት ውጤት ሥዕሎቹ ሉቃስ በነበረበት በመጀመሪያው ምእት ዓመት የተሳሉ ሳይሆኑ በመካከለኛው የክርስትና ዘመን የተሳሉ ይመስላሉ ብለው ገምተዋል ።

ሆኖም ይህ ምርመራ የሉቃስን ሠዓሊነት አያለውጠውም ።

በክርስትናው የሥዕል ትምህርት ቤት ቅ/ ሉቃስ ክንፍ ያለው በሬ (ላም) ባጠገቡ እንዳለ ሆኖ ይሣላል ። የሥዕሉም መግለጫ «ዘላህም ሉቃስ) ይላል ። ይህም ቅዱስ ሉቃስ ክርስቶስ በላሞች በረት መወለዱን ከሌሎች ወንጌላውያን ሁሉ ተለይቶ ገልጦ መጻፉን ያመለክታል ። በተጨማሪም የክርስቶስን መሥዋዕትነት በላም ፍሪዳ መስሎ መናገሩን ያስረዳል ። ይህንም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሲገልጡ «ሉቃስ ዘላህም ይባላል የመድኃኒታችንን መሥዋዕትነት ሐዲስዋ እምቦሳ በወለደችው በንጹሕ ላም ፍሪዳ መስሎ ይናገራል » ብለዋል ።

ቅዱስ ሉቃስ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻ ሕይወቱ ሚስት ያላገባ ንጹሕ ድንግል ነበር ። ይህ ሁኔታ በአንድ ሀሳብ ሆኖ ወንጌልን ለማስተማር ረድቶታል ። «ያላገባ ጌታን እንዴት ደስእንደሚያሰኝ የጌታን ነገር ያስባል ያገባ ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንደሚያሰኝ የዓለምን ነገር ያስባል» ተብሎአልና (፩ ቆሮ፯፤ ፴፪—፴፫)።

ከመካከለኛው የክርስትና ዘመን ጀምሮ ሉቃስ የዶክተሮችና የሠዓሊዎች ጠባቂ ቅዱስ እየተባለ ይጠራል ። ክርስቲያን ዶክተሮችና ሠዓሊዎች ያከብሩታል ። ከእነርሱ ብዙዎቹ በስሙ ይጠሩበታል ።

ሐዋርያውና ወንጌላዊው ሉቃስ ስለ ክርስቶስ በመመስከሩ ወንጌልን በማስተማሩና በመጻፉ አረማውያን እንዳይናገር ምላሱን እንዳይጽፍ ጣቱን ቆርጠው አሰቃይተውታል ። በዚህም ምክንያት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥቅምት ፳፪ ቀን በሰማዕትነት አርፎአል ። ያረፈውም በመጀመሪያው ምእት ዓመት በ፹፪ ዓመት

(መጋቤ ጥበብ ??)



www.ethiopianorthodox.org

# «እሞሙ ለሰማዕት (የሰማዕታት እናታቸው)»

እናትነት ወይም አባትነት በሥጋ ወልዶ ፣ በግር በወተትና በፍትፍት በማሳደግ ብቻ አይደለም ። በቀለም ወልዶ በትምህርት ማሳደግም እናትና አባት ያሰኛል ። ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ወልዶ በትምህርት ያሳደገውን ደቀ መዝሙር ጢሞቴዎስን «ልጄ» ይለው ነበር ። ፩ኛ ጢሞ/ ፪ እና ፲፰ ። ፪ኛ ጢሞ ፩ ፣ ፪ ከዚህም ሌላ «አንድ ቀለም የነገረህ እንደ አባትህ ሁለት ቀለም የነገረህ እንደፈጣሪህ ይሁን» የሚል ትምህርተ ሐዋርያት ተጽፎ ይገኛል ይህም አባባል የቀለም እናትና አባት እንዴት መረዳትና መከበር እንደሚገባቸው የሚያስረዳ ነው ።

በሃይማኖት ወልደው በሥጋ ወደ ሙ የሚያሳድጉት የክርስትና እናትና አባትም በትምህርተ ክርስትና መሠረት በጥምቀት የተቀበሏቸውን ልጆች ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ተንከባክበው የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የተፈለገው እምላክን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያም « ለሰማዕታት እናታቸው» የምትባለው በምንና እንዴት እንደሆነ ነው ። በመሠረቱ «እምሙ ለሰማዕት» በማለት በዜማ ድርሰቱ ደጋግሞ ተናገረው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነው ።

ታዲያ እመቤታችን «የሰማእታት እናታቸው» ለምን ተባለች ተብሎ ሲጠየቅ ሰማዕትነት በእሳት በመቃጠል በሰይፍ በመመታት ፣ በጦር በመወጋትና ደምን በማፍሰስ ብቻ አይደለም ስለ ጽድቅና ስለ እግዚአብሔር ብሎ የትውልድ ሀገርንና ዘመድ አዝማድን ትቶ መሰደድም ሰማዕትነት ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ ሶስት አመት ከስድስት ወር ሙሉ በግብጽ አውራጃዎች ስደተኛ ሁና ኖራለች ። ከምድረ እሥራኤል (ከናዝሬት) ወደ ግብጽ ስትሰደድ እሾህ እየወጋት እንቅፋት እየመታት የቀን ሐሩር የሌሊት ቁርእየ ተፈራረቀባት ብዙ ጭንቅና መከራን ተቀብላለች ጽዋትወ መከራን በመቀበልና የትውልድ ሀገርን ጥሎ ወደ ባዕድ ሀገር በመሰደድ እመቤታችን የመጀመሪያዋ ስደተኛ ናት ።

በተሰደደች ጊዜ እጅግ አሳዛኝ የሆነ ረኃብና ጽም ችግርና ኃዘን የትዕግን ቤተ ሰቦች ተገዳርትና ሌላም ግፍ ተፈጽሞባታል ። ሰማዕታት ከክርስቶስ ሞት በኋላ በስሙ አምነው ወንጌልን ተቀብለው ለሌሎች ለማዳረስ በሚያስተምሩበት ጊዜ ለማእት እንሰግድም ክርስቶስን እንክድም በማለት ይቀበሉት ዘንድ ያላቸው ስደትና ፅዋትወ መከራ ሁሉ ጀማሪ በመሆንዋ « ለሰማእታት እናታቸው» ተባለች ብለው ኢትዮጵ



እመቤታችን ድንግል ማርያም ወደምድረ ግብፅ እንደተሰደደች ፤

ስለክርስቶስ፣ ስለ ጽድቅና መንግሥተ ሰማያት መሰደድ መራብ መጠማት በአደባባይ በሰው ፊት ቆሞ መወቀስ ፣ የመሳሰለውን ሁሉ መስማት ሰማዕትነት ነው ። ሰማዕታት ረሀብንና ጽምዕን ስደትንና እሥራትን ፣ እሳትንና ሰይፍን በትዕግሥት የሚቀበሉት ስለ ክርስቶስ ፍቅር አምላክነቱን እየመሰከሩ ቸርነቱን እያወሩ ወንጌልን እየሰበኩ ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስለ ክርስቶስ ብላ ክርስቶስን ይዛ

ያውያን ሊቃውንት ያስረዳሉ ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም በጌታችንና በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ከአጋጠሟት ኃዘናት መካከል አንደኛው በሆነው በዕለተ ስቅለቱ በከፍተኛ ጭንቀትና ኃዘን ላይ ሳለች ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳለ ለሚወድደው ደቀ መዝሙር « እነሆዋት እናትህ » በማለት የፍቅርና የአደራ እናት አድርጎ ሰጥቷታል ዮሐ/ ፲፱—፳፯ ይህም የእመቤታችን ፍቅርና የአደራ እናትነት ለ



ንስ ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖች ሁሉ ነው ። ሰማዕታትም በዮሐንስ አንፃር » እነሆ ልጆችሽ» ተብለው የተሰጡ የፍቅርና የአደራ ልጆችዋ ናቸውና »እሞሙ ለሰማዕታት እናታቸው» ትባላለች ።

የሶርያው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም «ተፈስሒ እቅድስት እሞሙ ለኵሎሙ ሕያዋን ፤ የሕያዋን ሁሉ እናታቸው ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ በማለት አመስግኗታል ። ኤፍ ፪ ፣ ፮ በዚህም ክፍል«የሕያዋን ሁሉ እናት» የተባለችበትን ሊቃውንቱ ሲያትቱ ቀደም እናትዋ ሔዋን የሕያዋን እናት ነበረች በኋላ ግን አምላክነትን በመሻት በሠራችው ስሕተት እመ ምውታን የሙታን እናት ሆናለች በማለት በእርስዋ ምክንያት ሞት በሰዎች ላይ ሠለጠነ ። ይሁን እንጂ በሔዋን ምክንያት የተዘጋው የገነት በር በእመቤታችን ምክንያት ተከፈተ በሔዋን ስሕተት የታጣው ሕይወት በእመቤታችን አማካይነት ዳግመኛ ተገኘ ። ኤፍሬም ፩፤፫ ።

ክርስቶስ ከእመቤታችን ተወልዶ ዳግማይ አዳም በመባልና ስደትን ፣ ሕማምንና ሞትን በመቀበል ዓለሙን ሁሉ ሕያው አድርጎታል ዓለሙን ሕያው ያደረገው ክርስቶስ የሕይወት ሁሉ ራስ ነው የሕይወት ራስ የሆነ ክርስቶስን በሥጋ የወለደችና ለድኅነተ ዓለም ምክንያት የሆነች እመቤታችን ድንግል ማርያምም የሕይወት መሠረት የድኅነት ጥንት ናት። «መሠረተ ሕይወት ማርያም ወጥንተ መድኃኒት ዘእምቀዲሙ ፣ የሕይወት መሠረት ፣ የደኅንነት ጥንት ማርያም ሆይ ዓለሙን ለማዳን ያማርሽውን እንቺን የፈጠረ እግዛእብሔር ስሙ ይመስገን» ሲል ኢትዮጵያዊው ደራሲ ይገልጻልና ። በአጠቃላይ ግን በሔዋን ስሕተት በሰዎች ላይ ተንሠራፍቶ የነበረው ሞተ ነፍስ ከእመ

ቤታችን በሥጋ በተወለደውበክርስቶስ ስለተወገደና ሔዋንም ከነልጆችዋ ተመልሳ ሕይወትን ስለአገኘች ድንግል ማርያምን ሊቁ የሕያዋን ሁሉ እናት» አሳት ይላሉ ። በዕርግጥም የሕይወት መገኛና የሕያዋን ሁሉ እናት ናት ።

ስለዚህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት የእመቤታችን የድንግል ማርያምን አማላጅነት የሚያምኑ ሁሉ «ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ ሰዓሊ በእንቲአነ ወልድኪ ይምሐረነ « እናታችን የጌታችንም እናቱ ማርያም ሆይ ልጅሽ ይቅር ይለን ዘንድ ስለእኛ ለምኝልን» እያሉ በእርስዋ ይማፀናሉ ወደ ጌታም ይጸልያሉ ። ምክንያቱም ክርስቶስ ከእርስዋ የነሳውን ሥጋና ደም ተቀብለው ሕይወትን አግኝተዋል፤ ከስደትም ተመልሰው ወደቀድሞ ቤታቸው ወደ ገነት ገብተዋልና ነው ።

ጌታችን ከእመታችን ከመወለዱ አስቀድሞ በኃጢአት ገዥነት አገብርት አዕማት (ባሮች) ይባሉ የነበሩ ወንዶችና ሴቶች የአዳም ልጆች ሁሉ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ባሕርይ ከተዋሐደና በጥምቀቱ ጥምቀትን ከቀደሰ በኋላ የልጅነትን መዓርግ አግኝተዋል ። ይህም ይታወቅ ዘንድ ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ባርያ ጌታውየሚያደርገውን አያውቅምና ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ» ይላቸዋል ። ዮሐ/ ፲፭ ፣ ፲፭ እግዚአብሔር በመግቦቱ የፍጥረታት ሁሉ አባት ነው። እመቤታችን ድንግል ማርያም የሕይወት ራስ ጌታን ይዛ በመገኘትዋ የሕያዋን ሁሉ እናት ተብላለች ስለ ክርስቶስ ብላ ክርስቶስን ይዛ ወደ ግብጽ በመሰደድዋና ብዙ ጭንቅ መከራን በመቀበልዋ በክርስቶስ ፍቅር ተስበው ስለ ጽድቅና ፣ ስለት

ክለኛ ፍትሕ ለተሰደዱና ለሚሰደዱም እናታቸው ናት ።
ከዚህም ሁሉ ጋር በዮሐንስ አንፃር ለምእመናን ሁሉ የተሰጠች አማላጅነትዋ የማያሳፍር የፍቅርና የአደራ እናታችን ናት ።

መ/ ራደ አስረስ

## ደብዳቤዎች

( ከ፩ኛው ገጽ የዞረ )

እግዚአብሔር በሚል ስም ካህን ሆኖ ኖረ በማለት የአይሁድ ካህናት ይተርካሉ።ይህንንም ለማጽደቅና ሴም በአብርሃም ዘመን እንደ ነበረ ለማድ ረግ ከማየ አይህ በኋላ ከነበሩት የአበው ዘመን አንድ አንድ መቶ ቀንሰዋል እንዱን ቃይናንን ግን ፈጽመው አውጥተውታል በዚህ አቆጣጠር ሴም እስከ አብርሃም ይደርሳል ።

ከአይሁድ ሊቃውንት አንዳንዶች ግን መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም በተአምር የተገለጠ መልአክ ነው ስለዚህም አባትና እናት የሉትም ተባለለት ይላሉ ሌሎች ደግሞ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፲፰ ላይ እግዚአብሔር በሰው አምሳል ሆኖ ለአብርሃም እንደታየው ሁሉ ነገሥተ ሰዶምን ድል አድርጎ ሲመለስ ም በሰው አምሳል ታየው የሰላም ንጉሥ የጽድቅ ንጉሥ የተባለም ራሱ ግዚአብሔር ነው በማለት ሐሳባቸውን ይፈጽማሉ ።

በመጽሐፈ ስንክሳር ( ጳጉሜን )፫ ቀ/ ግን መልከ ጼዴቅ የሴም የልጅ ልጅ የቃይናን ልጅ ነው ተብሎ ተመዝግቦአል ይህም ትውፊት የተወሰደው ከጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ነው ።

ቅዱስ ቄርሎስ ደግሞ መልከ ጼዴቅ የካም የልጅ ልጅ መሆኑን ገልጠ ጽፎአል።እሱም እንዲህ ነው። «ካም ከነዓንን ይወልደል ከነዓን ሲዶንን ሲዶን ሳላህን፣ ሳላህ ሳሌምን ሳሌም መልከ ጼዴቅን ይወልዳል» ይላል። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም በዚህ አሳብ ይስማማሉ። በዚያም ሆነ በዚህ መልከ ጼዴቅ የክር

( ወደ፱ኛው ገጽ ዞሯል )



www.ethiopianorthodox.org

# ቅ ዱ ስ   ማ ቴ ዎ ስ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው ከ፲፪ ሐዋርያት አንዱ ቅዱስ ማቴዎስ ነው ። እርሱም ቀራጭ ነበር ።

ወንጌላዊው ማቴዎስ ለሐዋርያነት ከመመረጡ በፊት የመጠሪያ ስሙ ማቴዎስ ሳይሆን ሌዊ ተብሎ ይጠራ ነበር ይኸውም ወንጌላዊ ማርቆስ ስለማቴዎስ ጥንታዊ ስም ሲገልጽ በባሕር አጠገብ ሲያልፍ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮስ ልጅ ሌዊን እየና ተከተለኝ አለው» በማለት ሌዊ በሚል ስም መጠራቱንና የአባቱም ስም እልፍዮስ መሆኑን ጨምሮ ጽፎት ይገኛል ። ማር- ፪ ፡ ፲፬

ይህ ብቻ አይደለም፤ወንጌላዊው ሉቃስ በበኩሉ ስለማቴዎስ የመጀመሪያ ስም ሲጽፍ ሌዊ የሚባል ቀራጭ በመቀመጫው ተቀምጦ ተመለከተና ተከተለኝ አለው ። ተነሥቶም ተከተለው ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት ሲል ስሙንና ሥራውንም ጭምር አስፋፍቶ ገልጾአል ። ሉቃ- ፭ ፡ ፳፯

እንግዲህ ያዕቆብና ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጆች ፤ ጴጥሮስና እንድርያስም የዮና ልጆች እንደሆኑ ሁሉ ፤ ማርቆስ ሌዊ ወልደ እልፍዮስ ያለውን ይዘው ማቴዎስ የያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ወንድም መሆኑን የሚገምቱ አሉ ። ማቴዎስ ለሐዋርያነት የተጠራው በዚህ ዓይነት ሲሆን ፤ ኋላ ይህንን ዓለም ወንጌልን ለማስተማር በዕጣ ተከፋፍለው በሚሔዱበት ጊዜ ምድረ ፍልስጥኤም ለቅዱስ ማቴዎስ በዕጣ ደርሰዋለች ።



ቅዱስ ማቴዎስ ከዚያ ገብቶ ጌታችን ኢየሱስ ከተፀነሰበት ቀን ጀምሮ ወደ ሰማይ እስካረገበት ሰዓት ድረስ ያስተማረውን ትምህርት ያደረገውን ተአምራት ቢያስተምራቸው የፍልስጥኤም ሕዝብ ሁሉ በሕገ ኦሪት የነበሩት ወደ ሕገ ወንጌል (በአምልኮ ጣዖት) ጣዖትን ሲያመልኩ የነበሩት ደግሞ ጣዖቶቻቸውን እየሰበሩ አብያተ ጣዖቶችንም እየመዘበሩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው ተጠመቁ ። ቅዱስ ማቴዎስ በዚህ ሳይወሰን የወንጌል ትምህርት ወዳልደረሰባቸው አገሮች ለማዳረስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ለምሳሌ ፋርስ ባቢሎንንና ኢትዮጵያንም እንዳስተማረ በታሪክ ተጽፎ ይገኛል ። ቅዱስ ማቴዎስ ሀገረ ይሁዳንና ፍልስጥኤምን እንዳስተማረ አውሳብዮስ የተባለ ሊቅ ጽፎአል ።

ወንጌላዊው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን ማስተማሩን የሚገልጹ እነአውሳብዮስ ብቻ ሳይሆኑ ፤ ሌሎችም ታሪኮች በብዛት ይገኛሉ ። ለምሳሌ በዓረብኛ ቋንቋ ተጽፎ የታተመና ስንክሳር የተሰኘው መጽሐፍ የሚከተለውንቃል አስፍሮ ይገኛል ። «ወንጌላዊው ማቴዎስ ለማስተማር በታዘዘው መሠረት የወንጌልን ትምህርት በፍልስጥኤም ለሚኖሩ ሕዝብ ካስተማራቸውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሳምኖ በስሙ ካጠመቃቸው በኋላ ፤ ወደኢትዮጵያ ሔደ ይልና ከኢትዮጵያም ክፍላተ ሀገር ማቴዎስ ያስተማረበት ቦታ በትግራይ ክፍለ ሀገር መሆኑን ገልጾ እሱ ከዚያ ገብቶ በጣዖት የሚያመልኩ ሕዝብ አገኘና እነሱን መክሮና አስተምሮ ካጠመቃቸው በኋላ ይዘውት የነበረውን አምልኮተ ባዕድ አጥፍቶ የካህናተ ጣዖትት አለቃ የነበረውን ጳጳስ ሹሞላቸውና አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጽሙበትንም ቤተ ክርስቲያን ሠርቶላቸው ወደኢየሩሳሌም ተመ



ለሰ» ሲል በገጽ ፸፯ ላይ በሰፊው ያስረዳል።ስንክሣሩ ወንጌላዊው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ያስተማረበት ቦታ በትግራይ ክፍለ ሀገር መሆኑን ሲገልጽ በየትኛው አውራጃ መሆኑን አይናገርም ። ግን አንዳንድ ሊቃውንት በዓድዋ አውራጃ ከአክሱም ከተማ በስተ ደቡብ በሚገኘውና ልዩ ስሙ ናዕዴር በተባለው ወረዳ እንደሆነ ይናገራሉ። ወንጌላዊው ሚቴዎስ በፋርስና በኢትዮጵያ ማስተማሩ በታሪክ ተገልጿል።

ነቢዩ ዳዊት በ፸፩ኛው መዝሙሩ ፱—፲፩ ላይ «የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ ፤ የዓረብና የሳባ ነገሥታትም እጅ መንሻን ያቀርባሉ» ሲል በትንቢቱ እንደተናገረ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የተባሉት ከፋርስና ከባቢሎን የመጡ መሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን ፤ የዓረብና የሳባ የተባሉትም ከየመንና ከኢትዮጵያ የመጡ መሆናቸው ይነገራል ። ሲል የኢትዮጵያን ስም ጠርቶ መናገሩ ይህ ራሱ በቂ መረጃ ነው ። በሌላ በኩልም ሰብአ ሰገልን ከማቴዎስ በቀር ሌሎች ወንጌላውያን አያነሷቸውም ። ይህ ራሱ ማቴዎስን ብቻ ማውሳቱ በእነዚህ አገሮች ማስተማሩን ያመለክታል ።

ምክንያቱም ወንጌላዊው ማቴዎስ የሰብአ ሰገልን ታሪክ ከየት እንደመጡ ወዴትም እንደሔዱ ፣ ምን ዓይነት ሥራ ሠርተውም ወደየአገራቸው እንደተመለሱ በሰፊው ይገልጻልና ።

ማቴዎስ የጻፈውን ወንጌል አተኩረን ስንመለከተው ፣ ለአይሁድና በአይሁድ እምነት ለነበሩ ሕዝብ ይመስላል ። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ጠቅሷቸው የሚገኙት ቃላት ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ናቸውና ።

ቅዱስ ማቴዎስ ትምህርቱን እንዲ በቀሉትና ባለመሰልቸት እንዲሰሙትና ከዚህም ሌላ በመስማት ብቻ እንዳይቀሩ የሰሙትና የተማሩት ትምህርት በልባቸው ተቀርጾ እንዲቀር በማሰቡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውንም ሰባት ተአምራት በምዕራፍ ፰ ፤ እንዲሁም በምዕራፍ ፲፫ ያስተማራቸውን ሰባት ምሳሌዎች እንደሚከተለው ጽፏል ።

ይኸውም ለገበሬዎች የእግዚአብሔርን ቃል በዘር ፤ መንግሥተ ሰማያትን በእርሻ ፤ ለሴቶች በእርሾ ፤ ለነጋዴዎች በወርቅና በዕንቁ ፤ ለዓሣ አጥማጆች በመረብ ፤ ጻድቃንን በስንዴ ኃጥአንን በእንክርዳድ እየመሰለ ያስተምር ነበርና ።

ወንጌላዊው ማቴዎስ ሐዳችሁ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝንና መንፈሳዊ ተልዕኮውን ለመፈጸም እየተዘዋወረ ወንጌልን ሲያስተምር ከቆየ በኋላ ፤ ጥቅምት ፲፪ ቀን በመጀመሪያው ምእት ዓመት በሰማዕትነት እንዳረፈ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ።

በዚህም መሠረት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ጥቅምት ፲፪ ቀን በዓለ ዕረፍቱን ታከብራለች ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ ።

## ተወዳጁ ሐኪም ..

(ከ፩ኛው ገጽ የዞረ)

እድሜው ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ጥቅምት ፳፪ ቀን ወንጌላዊውን ሉቃስ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ቀድሞ በሕክምናው ደዌ ሥጋን ይፈውስ የነበረውይህ ጻድቅ ወንጌላዊ ዛሬም በአማላጅነቱ ምሕረት ከእግዚአብሔር እየለመነ ለኃጢአተኞች ሁሉ ሥርየትን የሚያሰጥ መሆኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አምና ታስተምራለች ። «አራቱ ወንጌላውያን ሆይ ስለ እኛ ለምኑልን አማልዱን» እያላች በምትጸልይበት ጊዜ ከወንጌላውያን አንዱ ሉቃስ ስለሆነ በዘወትር የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ላይ ሉቃስ ሳይጠቀስ አይውልም ዘወትር አማላጅነቱ የሚያስፈልግ ተዳወጁ የነፍስ ሐኪም (ዓቃቤ ሥራይ ዘነፍስ) ነውና ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## ደብዳቤዎች

(ከ፮ኛው ገጽ የዞረ)

ቶስ ምሳሌ የሆነ ታሪካዊ ሰው ነበረ «አባትና እናት የሉትም ፣ ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም » የተባለበት ምክንያት ግን ሐረገ ክህነቱ ከማን እንደሆነ ወደ ማን እንደ ተላለፈ ስላልታወቀ ነው ። ለምሳሌ አሮናዊው ሐረገ ክህነት ከያዕቆብልጅ ከሌዊ ጀምሮ እስከ አሁን ሳይቋረጥ በአይሁድ ዘንድ ይኖራል ። የመልከ ጼዴቅ ክህነት ግን እንዲህ አይደለም ከራሱ ብቻ ተጀምሮ በክርስቶስ የተተረጐመ ነውና

ሁለተኛም የመልከ ጼዴቅ ትውልዱ ከነገደ ሴም ሳይሆን ከነገደ ካም በመሆኑ በእሥራኤ ላውያን መዝገበ ታሪክ አልተጠቀሰም መጽሐፍ ቅዱስም በብዛት የሚናገረው ስለ እሥራኤል ሲሆን ያውም ስለተመረጡት ብቻ እንጂ ስለሌሎች ነገዶች አይናገርም ። በዚህ ምክንያት አባትና እናት የሉትም ተባለ ።

ከዚህም ሌላ እንደ አባቶች እንደ አብርሃም እንደ ይስሐቅ - - - እንደካህናትም እንደ ሌዊና እንደ አሮን የተወለደበትና የሞተበት ዘመን ተለይቶ ስላ ተጻፈ ፣ ሚስትም አግብቶ ልጆችን ስላ ልወለደ ለሕይወቱ መጀመሪያና ፍጻሜ የለውም ፣ ተባለ እንጂ መልከ ጼዴቅ የካም ዘር ነው ኢየሩሳሌምንም በአባቱ በሳሌም ስም ሰይሞ ይኖር የነበረ የሰላምና የጽድቅ ንጉሥ እንደሆነም ይታመናል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ( የ ወ ጣ ቶ ች ዓ ም ድ )

# ወጣቶች በመስቀልና በወርኃ ጽጌ

ከኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

መስከረም ፲፯ ቀን የጌታችንና የመድኃኒታችን በዓለ መስቀል በመሆኑ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ሁሉ ከደመራው ዕለት ጀምረው በዓሉን በየዓመቱ በደመቀ ሁኔታ ሲያከብሩት እንደሚኖሩ የታወቀ ነው ። ይልቁንም ወጣቶች እንደብሔራቸው ልማድ ባሕልና ቋንቋ መሠረት የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶችን በመጫወት የበዓሉን መታሰቢያ ያከብራሉ ።

በአንዳንድ አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች ሸለምላሚ የሆነ ዱላቸውን ይዘው በዘፈንና በጭፋር የመስቀልን በዓል የሚያከብሩ ሲሆን ፣ በሌላው አካባቢ ደግሞ ጠንካራና ፈጣን የሆኑ ፈረሶችን አዘጋጅተው የጉግስ ጨዋታ በፈረስ ላይ ሆነው የጦር ውርወራ ትርኢት በማሳየት በዓሉን ሲያከብሩ ይታያሉ ። በብዙ ቦታዎች እንደሚታየው ግን ወጣቶች ተመራርጠው የሆያሆዬ ጨዋታና ጭፋር የሚጀምሩት በመስቀል ዋዜማ የደመራ ዕለት ነው ። ወጣቶቹ ከዚያን ዕለት ጀምረው ቀን እየቆጠሩ ሰዓት እየመረጡ በጥቅምት ወር ማለት ወርኃ ጽጌን በሙሉ ማታ ማታ በየሰው ቤት እየሔዱ በመዝፈንና በመጨፈር እየተጫወቱ ገንዘብ ይሰበስቡና « በጥቅምት አንድ አጥንት » በሚለው ዘይቤ በመጠቀም ሰንጋ ገዝተው፤ያንን አርደው ሥጋውን በልተው ቆዳውን ለጠፍር ይከፋፈላሉ ። ወጣቶቹና ጉልማሶቹ ወደየሰው ቤት እየሔዱ የሆያሆዬ ጨዋታ በሚጫወቱበት ወቅት የባለቤቶቹን ስም በየተራ እየጠሩ ስለሚያሞግሱ የገንዘብ ስጦታ ያገኛሉ ። ከዚያም አልፎ ሙክት እንኳ የሚሰጡ ሰዎች እንደነበሩ ይነገራል ። ከዚህም የተነሣ ወጣቶቹ ሙክቱን ከተቀበሉ በኋላ

«የኔማ አቶ እገሌ የሰጠኝ ሙክት
በለጭማ ነው ባለምልክት
በአንድነት አርደን ነገ ጧት እንክት» እያሉ በደስታ የሚጨፍሩ ሲሆን ብር የሰጣቸውን ደግሞ

«ለዝና ብሎ ለመስጠጫ
ጉኔን ሰበረው በብር ጡጫ» እያሉ ያሞግሱ ነበር ይባላል ። ይህም ማርትሬዛ በመባል የታወቀው ጠገራ ብር በገበያ ላይ በዋለበት ዘመን የተዘፈነ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል ። እነዚህን ለማስታወስ ያህል ጠቀስናቸው እንጂ ግለሰቦችንና ጠቅላላውን ኅብረተሰብ የሚመለከቱ በርካት ያሉ የሙገሳ የስድብ ግጥሞች እንዳሉ የታወቀ ነው ።

ይህ በጥንታውያን ወጣቶች ሳይሆን የነበረና ዛሬም አልፎ አልፎ የሚታይ ጥንታዊ ባሕል ሲሆን ፣ የቆሎ ተማሪዎች ደግሞ «ተስዒነነ በመባል የሚታወቅ ጥንታዊ ባህል ነበራቸው ። ይህም ባሕል ይታይ የነበረው ከመስቀል ዕለት ጀምሮ እስከ ወርኃ ጽጌ መጨረሻ ነው ። ይህም በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ በጥቅምት ወር ውስጥ የሚካሔድ ነው ለማለት ይቻላል ።

በዚህ ወቅት ወጣት ካህናትና የቆሎ ተማሪዎች ተመራርጠው አምመው ጠምጥመው ከበሮና ጽናጽል መቋሚያና መስቀል ይዘው በደመራ ዕለት ጀምሮ፤ቅዳሜና እሑድ እንዲሁም የአጥቢያቸው ታቦት በሚከበርበት የበዓል ቀን ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምረው በየመንደሩ እየሔዱ ተሰዒነነ ዘወንጌል ቃለ ኅቡረ ተመርጉዘነ መስቀለ (የወንጌልን ቃል ተጫምተን በአንድነት መስቀሉን ተመርኩዘን መጣን)የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ መስቀሉን አስቀድመው በየመንደሩ ይገባሉ ። ከዚያም ሌሎችን መዝሙሮች በየተራ በመዘመር ደመቅ ያለ ቸብቸቦና ሽብሸባ ያሰማሉ ።

ለምሳሌ፦—«ጽጌ ገነት ደብረ መድኃኒት ፣ ሰላማዊት »

መዓዛ አፉሃ ከመኮል ፣ ወዴና አልባሲሃ፤ከመ ዔና ስሒን»የሚሉትን መዝሙሮች እያሸበሸቡ ውዝዋዜው ደመቅ ሲል ዘፈንም ይታከልበትና፤ግጥም እየደረደሩ ባለቤቶችን ማሞገስ ይጀምራሉ ። ምእመናኑ ማለት የቤቱ ባለቤቶች በዚህ ጊዜ የወጣትን ካህናቱን ወረብ በማዳመጥና በጣዕመ ዜማው በመመሰጥ በሙገሳውም በመደሰት በአቅማቸው መጠን ተገቢ የሆነ ስጦታ ያደርጋሉ ።

የስጦታው ዓይነት ቀደም ባለው ዘመን አሞሌ ጨው ፣ ኋላም ጠገራ ብር ሲሰጥ የቆየ ሲሆን ሌሎችም የስጦታ ዓይነቶች ነበሩ ።

ለምሳሌ፦—ሴቶች ጋቢና ኩታ ሲሰጡ ወንዶች ደግሞ ካባና ሻሽ ይሰጡ እንደነበረ የዓይን ምስክር ሆነው በጊዜው የነበሩት ሁሉ ይናገራሉ ። ይህ ብቻ አይደለም ። የፍየል ወጠጤ ፣ ሙክት ፣ ወይፈንና በሬ ሳይቀር የሚሰጡ እንደነበሩም የታወቀ ነው ። ሁለትና ሦስት ማድጋ እህልና ከዚያም በላይ የሚሰጡም ነበሩ። እንዲሁም ቆለኞች ደግሞ ጥጥ ከብት አርቢ የሆኑ ዘላኖች ደግሞ ቁም ከብት እርጎና ወተት ጭምር ይሰጡ እንደነበረም ይነገራል።ይህ ወዲያውኑ በወቅቱ የሚሰጥ ስጦታ ሲሆን በቂ ሀብት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ግን በዕለቱ ከሚሰጡት ስጦታ ሌላ ቀን ቀጥረው ሰንጋ አርደውና ጠላ ጠምቀው ጠጅ ሳይቀር እንደችሎታቸው መጠን ግብዣ አዘጋጅተው ፣



«ተስዒነነ» ለማለት በቤታቸው የመጡትን ተማሪዎችና ካህናት በጠቅላላ ጠርተው ይጋብዙ እንደነበርም አባቶች ይናገራሉ ።

በአጠቃላይ ሁኔታውን ለመግለጥ ተማሪዎቹ « ተሰእነነ » የሚሉት በከበሮና በጽናጽል ከመሆኑም ሌላ፤መስቀል አስቀድመው ክርስቶስን እየሰበኩ በመሆኑ ምእመናኑ ያላቸውን ከመስጠት ዓይነፍጉም ። ይህም ፤—

፩- መስቀል ከቤታቸው ድረስ በመምጣቱና ቤታቸው በመስቀል በመባረኩ

፪- ከቤታቸው ውስጥ ስመ እግዚአብሔር በመጠራቱ ቤታቸው እንደሚባረክ ስለሚያምኑ ፤ መዝሙር በመዘመሩና በጣዕመ ዜማው ልባቸው ስለሚመሰጥ ፤

፫- ስማቸው በመዝሙር በመነሣቱና በመሞገሳቸው ፤

፬- ተማሪዎችን በምክንያት ለመርዳት በጎ ፈቃድ ስላላቸው ነው ።

እንደተባለውም የእግዚአብሔር ቃል በቤታቸው በመነገሩና በመዘመሩ ረድኤተ እግዚአብሔር —በቤታችን ያድራል ብለው ፍጹም ተስፋ ስለሚያደርጉ በእምነታቸው መጠን እዝመራቸው ፤ ከብቶቻቸውና ልጆቻቸው ይባረካሉ ። ቤታቸውም የበረከት ቤት ይሆናል ።

በመጨረሻም ተማሪዎቹ የአቀዱቸውን መንደሮች ሁሉ አዳርሰው ካበቁ በኋላ በስጦታ ያገኙትን ሀብት በአንድ ላይ በማሰባሰብ እህሉን ጥጡን ፤ ከብቱንና የመሳሰለውንም ሁሉ ሸጠው ገንዘቡን በማዳመር እኩል ይካፈሉና እያንዳንዳቸው በደረሳቸው ገንዘብ ልብሳቸውን ይለብሱበታል። መጽሐፍ ለሚጽፉም ብራና ይገዙበታል ። የተረፈውንም ለባለ ችግራቸው ያውሉታል ። ይህ በቀድሞ ጊዜ የቆሎ ተማሪዎች እየዘመሩ እየወረቡና እያሸበሸቡ የሚዝናኑበትና ሌሎችንም የሚያስደስቱበት መንፈሳዊ ባሕል ነበር ። በሌላ በኩልም በተዘዋዋሪ ችግራቸውን የሚወጡበት መንፈሳዊ ፕሮግራም ነበረ ለማለት ይቻላል ። ዛሬም ቢሆን እንደጥንቱ አይጉላ እንጂ አልፎ አልፎ ይደረጋል ። ጥንታውያን ተማሪዎች እስካሉ ድረስ የተማሪዎች ባሕልና ልማድም ጸንቶ ይኖራልና ።

# የጽጌ ማኅሌትና የጽጌጾም መቼ ተጀመረ?

ከመስከረም ፳፮ እስከ ሕዳር ፭ ያለው አንድ ወር ከአሥር ቀን ወይም አርባ ቀን ወርሐጽጌ ተብሎ ይጠራል ።በነዚህም ቀናት በየቤተክርስቲያኑ የሚነበቡት ምንባቦች፤ የሚዘመሩት መዝሙሮች፤ የሚሰበከው ስብከት፤ የሚቆመው ማሕሌትበጠቅላላ ላው የሚነገረው ስብሐተ እግዚአብሔር ሁሉ ሰማይ በከዋክብት ምድር በጽጌያት አሸብርቀው የሚታዩ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው ።

ይህም ወርኃ ጽጌ በጉምና በጭጋግ ተሸፍኖ በጥቁር ደመና ተጋርዶ የነበረው ሰማይ በፀሐይ ተለውጦ፤ በጭቃ ተውጦ የነበረው መሬት በአበባ ተሸልሞ በጠቅላላው ዛፉ፤ ተራራው አበባ ብቻ ሆኖ ሜዳው ሁሉ አረንጓዴ ለብሶ የሚታይበት ያበባ ወራት በመሆኑ ሰውን በተስፋ ለተስፋ ይጋብዛል ። የአበባውም ሽታ ስለሚያውድ ሕይወትን ያስደስታል።

ቀደም ብሎ ይህንን የተገነዘበው ጠቢቡ ሰሎሞን «እነሆ ክረምቱ አለፈ ዝናብም አልፎ ሄደ ። አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ ። የዜማም ጊዜ ደረሰ ፤ የቁርዩውም ቃል በምድራችን ተሰማ፤ በለሱ ጐማራ፤ወይኖቹም አበቡ፤መዓዛቸውንም ሰጡ» ሲል የሚታየውን የአበባ ድምቀትና የመዓዛውንም ለዛ ተናግሮአል መኃልየ መኃልየ ምዕራፍ ፪ ከቁጥር ፲፩—፲፫

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሲያስተምር «ስለ ልብስ ለምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ ፤ አይደክሙም ፤ አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ ሰሎሞን እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም» ሲል አበቦች በሕብረት ቀለማቸው፤ በውበታቸውና በመዓዛቸው ተመሳሳይ እንደሌላቸውና አስደሳች መሆናቸውንም ተናግሮላቸዋል ።

ማቴ ፮፥፳፰—፳፱

ቅዱስ ያሬድም « እንዘትብል ነዓ ወልድ እሁየ ንጻእ ሐቅለ ንረአይ ለእመ ጸገየ ወይን ወለእመ ፈረየ ሮማን ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ ወልድ እሁየ ቃልከ አዳም» ትርጓሜው ልጂ ወንድሜና ወደ ሜካ እንውጣ ወይኑ አብቦአል ሮማኑም አፍርቶአል እናይ ዘንድ እያለችና ሙሽራዋ ቃልህም ጥሩ ነው ብላ አመስገነችው በማለት ክርስቶስን ሙርዓዊ ቤተ ክርስቲያንን በመርዓት መስሎ ተናግሯል እንዲሁም አሰርገወ ሰማየ በከዋክብት ወምድረኒ በስነ ጽጌያት ትርጓሜው በስነ ፍጥረት የሚታወቀውና የተገለጠው እግዚአብሔር ሰማይን በከዋክብት ምድርንም በአበቦች ሸለመ ሲል ሙሴ የጻፈውን በማስመልከት በዜማ ድርሰቱ ገልጿል ።

በወርኃ ጽጌ ለሚከናወነው መንፈሳዊ አገልግሎት መነሻው «መልአኩ ሕፃኑንና እናቱን ወደ ግብጽ ይዘሐቸው ሽሽ የሕፃኑን ነፍስ ሊገሉት ይፈልጋሉና» ሲል ለዮሴፍ በሕልሙ በነገረው መሠረት ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱንድንግል ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ መሰደዱና እመቤታችንና ሕፃኑ ሶስት ዓመት ከመንፈቅ በስደት ከኖሩ በኋላ ወደ አገራቸው ወደ ናዝሬት የመመለሳቸው መታሰቢያ ነው ።

እመቤታችንም ከስደት ከተመለሰች በኋላ ከሐዋርያት ጋር እያሌ ዘመን ኑራለች ይሁን እንጂ ሐዋርያት ሰባቱን አጽዋማት በሲኖዶስ ሲወስኑ የጽጌ



www.ethiopianorthodox.org

ጾም እንዲጾም ሲሉ አልወሰኑም ሶስት መቶ አስራስምንቱ ሊቃውንትም የሐዋርያትን ውሳኔ እንደገና ሲያጸድቁ ስለ ጽጌ ጾም ግን ያነሱት ነገር የለም። በዚያን ዘመን የነበሩት የመጀመሪያዎቹ የግብጽ መነኮሳትም ቢሆኑ የጽጌን ጾም የፈቃድ ጾም አድርገው ይጾሙት እንደነበር መረጃ አልተገኘም።

ስለ ማህሌተ ጽጌም ቢሆን ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት የመጣልን ከኮፕት ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ማህሌተ ጽጌ በኮፕት ቤተ ክርስቲያን በወርኃ ጽጌ ይቆም እንደነበር መረጃ አልተገኘም። እንኳንስ ማህሌት መቆሙ ቀርቶ ከድጓም በቀር ዜማ አልነበራቸውም ያሬድ በነበረበትም ዘመን ቢሆን በወርኃ ጽጌ ማህሌተ ጽጌ ይቆም እንደነበር መረጃ አልተገኘም ።

የጽጌ ጾምና ማህሌተ ጽጌ መቼ ተጀመረዞተባለ እንደሆን የአቡነ ዜና ማርቆስ ገድል እንደሚከተለው ያብራራል «አቡነ ዜና ማርቆስ የምሁርን ሕዝብ አስተምረውና አሳምነው ካጠመቁ በኋላ እንደገና ለማስተማር ወደ ይፋት ሄዱ ። በዚያም ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ስለኛ ኃጢአት ተሰቅሎ ሞተ በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተነግ እያሉ ሲያስተምሩ ፩ አይሁዳዊ ሰግ ይህም አይሁዳዊ እንዴት እንዲህ እያሉ ያስተምራሉ ሲል ተቃውሞ አቀረበባቸው እሳቸውም የብሉይና ሐዲስ አዋቂና ዘዴኛ ስለነበሩ የሚከተለውን ጥቅስ እየጠቀሱ ያስረዱት ጀመር።

«ትወፅዕ በትር እምሥርወ እሴይ ፤ ወየዓርግ ጽጌ እምጉንዱ» ከእሴይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዱም አበባ ይወጣል ያቆጠቁጣል በትር እመቤታችን ድንግል ማርያም ስትሆን ጽጌ ደግሞ ከእስዋ የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲሉ አቡነ ዜና ማርቆስ በትንቢተኢሳይያስ ምራፍ ፲፩ ቁ፩ ያለውን ትርጓሜውንና ምሥጢሩን ዘርዝረው ባስረዱት ጊዜ አይሁዳዊው አምኖ ትምህርታቸውን ተቀበለ።

አቡነ ዜና ማርቆስም አዲስ ኪዳን አስተምረው አሳምነው ካጠመቁት በኋላ አመነከሱት ሥሙንም ጽጌብርሃን ብለው ሰየሙት አባ ጽጌ ብርሃንም ምሁረ አሪት ስለ ነበር መጻሕፍተ አዲሳትን ለማጥናት ምቹ ሆነለት ቀጥሎም ከሳቸው ጋር እየተዘዋወረ ወንጌልን ያስተምር ጀመር።

ይህንንም ከፈጸመ በኋላ እንደ መዝሙረ ዳዊት መቶ አምሳ አድርጎ ማህሌተ ጽጌን ደረሰ አባ ጽጌ ብርሃን ይህንን በደረሰበት ጊዜ የወረ ኢሉ ተወላጅና የደብረ ሐንታው አባ ገብረ ማርያም አግካሪው ነበር ድርሰቱንም ሲደርስ ቤት እየመታና በአምስት ስንኝ እየከፋፈለ ነው።

ይህም የማህሌተ ጽጌ ድርሰት በሰምና ወርቅ የተደረሰ ሆኖ እበባን ሰምጌታና እመቤታችንን ወርቅ እያደረገ ስለሚናገር ለሚያነበውና ለሚጸልየው እጅግ ያዐደስታል ። በዚህ አኳኋን «አባ ጽጌ ብርሃንና አባ ገብረ ማርያም ከመስከረም ፳፮ ቀን እስከ ሕዳር ፭ ቀን ድረስ ማኅሌተ ጽጌ ለመቆምና የጽጌን ጾም ለመጾም በየአመቱ በደብረ ብሥራት እየመጡ ይሰነብቱና ቍስቋምን ውለው ወደየ በአታቸው ይመለሱ ነበር»

እንግዲህ አባ ጽጌ ብርሃንና አባ ገብረ ማርያም የጽጌን ማህሌት መቆም የጽጌን ጾም በፈቃድ መጾም የጀመሩ እነሱ ናቸው ። ዘመኑም በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ አባ ጽጌ ብርሃን በሰይፈ አርእድ ዘመነ መንግሥት ለደብረ ብሥራትና ለደብረ ሐንታ ሊቀ ካህናት ሆኖ ተሹሞ እንደነበር ገድሉ ይናገራል ።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የጽጌን ማህሌትና የጽጌን ጾም የጀመሩ እቴጌ ምንትዋብ ናቸው ይላሉ እሳቸውም ድንግል ማርያምን ይወዱና የቁስቋምን ቤተ ክርስቲያን አሰርተው ስለነበር በወርኃ ጽጌ ማህሌት ለሚቆሙት ካህናት ምሳ ኢያበሉ የጽጌን ጾም ከመጾም በቀር እሳቸው ጀመሩ የሚል ጽሑፍ አልተገኘም የጀመሩት ከላይ የተጠቀሱት ናቸው።

ከዚያ ወዲህ ግን ጥቂት በጥቂት እያሉ አብያተ ክርስቲያናት በወርኃ ጽጌ የጽጌን ማህሌት መቆም ጀመሩ። ጥቂት መነኮሳትና አንዳንድ አግኞችም በገዛ ፈቃዳቸው የጽጌን ጾም መጾም ያዙ በዘመናችን ግን በወርኃ ጽጌ የጽጌን ማህሌት መቆም ስለተለመደ ከማታው በሶስት ሰዓት ይደወላል ሴቱ ወንዱ ፤ ትንሹም ትልቁም ይሰበሰባል ማኅሌተ ጽጌው እየተዜመ፤ አስፈላጊ የሆነው በጸናጽል በከበሮ እየተመረገደና እየተወረበ እየተሸበሸበ እስከ ጠዋቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ ተቁሞ ያድራል

ወርኃ ጽጌ እስካለቀ ድረስ በየሳምንቱ ያለውን እሁድ ቀሳውስቱ በመከፋፈል ንስሀ ልጆቻቸውን አረቂ፤ ጠጅ፤ ጠላ፤ እንጀራ፤ ወጥ፤ ፍሪዳ በማስመጣት ሲያገለግሉ ያደሩትን ካህናትና ሊያስቀድሱ የመጡትን ምዕመናን ይጋብዛሉ ።

አሁን ግን ካህናቱም ሆኑ ምዕመናኑ የሰበካ ጉባኤ አባሎች በመመካከር እሕል ውኃ ቀርቶ ለቤተ ክርስቲያን ማደሻ፤ የጎደለ ንዋየ ቅድሳት ማሟያ፤ የካህናት ደመወዝ እንዲሆን ወደ ገንዘብ አስተዋጽኦ እየለወጡት ነው ይህም የሚደገፍ ነው ይህንን የማያደርጉ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩ ወደፊት ይህንን አርአያ እንደሚከተሉ ተስፋ አለን ካህናት ሰፊ ደሞዝ ካገኙ የጽጌ ማኅሌትን በድምቀት እንደሚቆሙ ይታመናል የጽጌም ጾም ውዴታ እንጂ የግዴታ አይደለም ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ





# ቅዱስ ጋብቻ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንካኋት ሰባት ምሥጢራት አንዱ ጋብቻ ነው። ይህም በቤተ ክርስቲያን አጠራር ምሥጢረ ተክሊል ይባላል ። ጋብቻ በጾታ የተለያዩ ሁለት ወጣቶችን በኑሮአቸው በአካሄዳቸውና በአስተሳሰባቸው አንድ የማድረግ ፤ የማጣመር ፤ ከሁለት ግለሰብነት ወደ አንድ ቤተሰብነት የመለወጥ ኃይል ያለው ስለሆነ ምሥጢር ይባላል ።

ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከፈጠረ በኋላ ብቸኝነቱን አይቶ ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት በማለት ፤ ከአዳም ግራ ጐን አጥንት ወስዶ ሴትን (ሔዋንን) ፈጠረ አዳም ይህች አጥንት ከአጥንቴ ፤ ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት እርሷ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል ሲል ጋብቻን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈጸመ ጋብቻም የተቀደሰና የተከበረ በመሆኑ ፤ ሁለት የተነጣጠሉ ግለሰቦችን አንድ የሚያደርግ ቅዱስምሥጢር ነው ዘፍ ፪ ፣ ፲፰—፳፭

እንደዚሁም የጋብቻን ቅዱስነት ለማረጋገጥ ሲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ሠርግ ቤት ተገኝቶ የመጀመሪያውን ተአምር እንዳደረገና ጋብቻንም እንደባረከ በዮሐንስ ወንጌል ፪ ፣ ፩—፯ ላይ ተገልጾአል ።



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጸሎተ ተክሊል ሲያደርሱ ፤

ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተ ፤ ክቡር ዓላማ ያለው ቁም ነገር ነው ለዚህም ዋና ማስረጃ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል ወደዚህ ዓለም መጥቶ ዓለምን እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ ፈሪሳውያን የጋብቻን ነገር በማናናቅ ሊፈትኑት«ሰው ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን ? ብለው ጠየቁት እርሱም መልሶ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን ? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም እግዚአብሔር ፤ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየውም» (ማቴ ፲፱ ፣ ፫—፯) በማለት ጋብቻ ሰው ሰራሽ ያለመሆኑን ፤ ለፍላጐት ማርኪያ ብቻ በልማድ የሚከናወን ፤ በተፈለገም ጊዜ የሚፈርስና የሚናድ አለመሆኑን ለፈሪሳውያን በሰጠው መልስ ላይ በግልፅ አስረድቷል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ጋብቻን አስመልክቶ ባልና ሚስት በኑሮአቸው ምን ዓይነት ሥነ ሥርዓት መጠበቅ እንዳለባቸው ለኤፌሶን ሰዎች መልእክቱን ሲያስተላልፍ «ባሎች ደግሞ እንደገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል ። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና ። --- ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱንም ይተዋል ። ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ፤ »ካለ በኋላ የጋብቻን ምሥጢር ታላቅነት ሲያበስር« ይህ ምጢር ታላቅ ነው እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለቤተ ክርስቲያን እላለሁ ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት ሚስቱም ባልዋን ትፍራ» (ኤፌሶን ፭ ፣ ፳፰—፴፫) በማለት ጋብቻ የቤተሰብ መመሥረቻ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የሥነ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ከላይ በተጠቀሰው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ለመረዳት ይቻላል ።

በዚህ መሠረት ወ/ንብረት አበበና



www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ለይኩን ብርሃኑ የጋብቻቸውን ሥርዓት ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ·ም በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ፈጽመዋል እነዚሁ ሁለት ወጣቶች ከልጅነታቸው ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት ታንጸው ያደጉ ከመሆናቸውም በላይ በአሁኑም ጊዜ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በመሳተፍ ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱና የሚያበረክቱ ወጣቶች ናቸው ።

ዲያቆን ለይኩን ብርሃኑ ቀደም ሲል ከ፲፱፻፶፯ ዓ·ም ጀምሮ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በዲቁናና በስብከተ ወንጌል ሥራ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ሲያገለግል ቆይቶ በ፲፱፻፷፬ ዓ·ም መጀመሪያ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ሩማንያ ተልኮ በቲኦሎጂ የማስትሬት ዲግሪ በመቀበል ወደ እናት ሀገሩ ፤ ከተመለሰ በኋላ በ[illegible] ቤት ክህነት [illegible] መምሪያዎች ተመድቦ ከማገልገሉም በላይ የአርሲ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ በመሆን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተመደበበትን ሥራ በከፍተኛ ታማኝነት አከናውኗል ። በአሁኑም ጊዜ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተዛውሮ የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዋና ጸሐፊ በመሆን ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ የሚገኝ ወጣት ነው ።

ወ/ት ንብረት አበበም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን በተቋቋሙት መንፈሳውያን ማኅበራት በተለይም በኡራኤል የሰንበት ት/ቤት በዓባልነትና በልዩ ልዩ ከፍተኛ ኃላፊነት ስታገለግል የኖረችና አሁንም በማገልገል ላይ ያለች ስትሆን በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ የሰንበት መምህርት በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከተችና በማበርከት ላይ የምትገኝ ናት በተጨማሪም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት አማካይነት እየተዘጋጀ በሚወጣው « ትንሣኤ » መጽሔት በተለያዩ ርዕሶችና እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ የቤተሰብ ዓምድ የሚለው ርእስ በትርፍ ጊዜዋ ሥነ ጽሑፍን በማቅረብ ለቤተ ክርስቲያናችን እያሌ ትሩፋትን በማበርከት ላይ ያለች ወጣት ነች ።

ከላይ ስማቸውና የሕይወት ታሪካቸው በአጭሩ የተጠቀሰው ሁለት ወጣቶች በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በተክሊልና በቁርባን የጋብቻቸውን ሥነ ሥርዓት በፈጸሙበት ዕለት ፩ኛ/ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ፤ ፪ኛ/ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤ ፫ኛ/ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ፬ኛ/ ብፁዕ አቡነ ገሪማ በሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ተገኝተው የሁለቱን ወጣቶች ሥርዓተ ተክሊል አድርሰዋል ። የሥርዓተ ተክሊሉና ቁርባኑ ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመ የቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን መዘምራንና የሰንበት መምህራን በካቴድራሉ ተገኝተው « ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ ፤ ትቄድሶ መርዓት የሚሉትን የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መዝሙሮችን በመዘመርና በማሸብሸብ ለበዓሉ ከፍተኛ ድምቀትን ሰጥተውታል ። በካቴድራሉ የተዘጋጀው መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመም ወደ መንበረ ፓትርያርክ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ጉዞ ተደርጐ ሙሽሮቹ መንበረ ፓትርያርኩ አዳራሽ ቅጥር ግቢ እንደደረሱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመዝሙርና በሽብሸባ ከተቀበሏቸው በኋላ በአዳራሹ ውስጥ የተዘጋጀው የቁርስ ግብዣ ፕሮግራም ቀጠለ በግብዣውም ላይ ልዩ ልዩ መንፈሳውያን ሥነ ጽሑፎችና መዝሙሮች በአበው ሊቃውንትና በሰንበት መምህራን እንደዚሁም በኡራኤል ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ተሰምቷል።በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተዘጋጀው ፕሮግራም ከጧቱ ልክ በስድስት ሰዓት ከተፈጸመ በኋላ ወደቀኑ ዝግጅታቸው አምርተዋል ።

ሁለቱ ሙሽሮች « እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም » የሚለውን አምላካዊ ቃል ተረድተውና በሙሉ ልብ ተፈቃቅደው ፤ የጋብቻንም ትርጉም ጠንቅቀውና አውቀው ሥርዓተ ጋብቻቸውን የፈጸሙ ስለሆነ ኑሮአቸው ሁሉ የተቃና እንደሚሆንላቸው ተስፋ በማድረግ መልካም ጋብቻ እንዲሆንላቸው ከልብ እንመኝላቸዋለን ።

በላይ ተገኝ

# የመጀመሪያው መርከብ ሠሪ

የሰው ልጅ እንደዛሬው በሳይንሳዊ ጥበብ ሳይራቀቅ አንዱ ከሌላው ተምሮ ሳያውቅ በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ የመጀመሪያውን ነፍስ አድን መርከብ የሠራው ጻድቅ ኖኅ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ዘፍጥ ፮ ፤ ፲፬—፲፮

የእግዚአብሔር መልእክተኛ ከአዳም ፲ኛ ትውልድ የሆነ ወደ ፭፻ ዓመት የሚጠጋውን ኖኅን አገኘ ኖኅ በክፉ ኅብረተሰብ መካከል ቢኖርም በክፋት ያልተበከለ ጻድቅ ሰው በመሆኑ በአንዲት በታሪክ ዘንድ በማትረሣ ቀን እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው «የሥጋ ሁሉ ጥፋት በፊቴ ደርሷል። ምድር ኃጢአት ሠርታለችና እኔም እነሆ የጥፋት ውሃ በመሬት ላይ አመጣለሁ የሕይወት ነፍስ ያለውን ሁሉ ሥጋ ከሰማይ በታች አጠፋ ዘንድ በምድር ያለው ሁሉ ይሞታል»

ኖኅ በዙሪያው ያሉ ሰዎች በክፋታቸው ቅጣት እንደሚያገኛቸው ቢያውቅም ጻድቅ ሰው በመሆኑ ይህን ቃል ሲሰማ ያዝን ነበር ።

በመሠረቱ ኖኅ ፍጡር በመሆኑ ይዘን እንጂ እግዚአብሔር ቅጣት አመጣለሁ ቢልም እንኳን የፈለገ ሁሉ የሚድንበትን መንገድ እንደዘመናዊ የጦር መርከብ ያለ እንዲሠራ ኖኅን አዘዘው ።

የሠራውም መርከብ ርዝመቱ ፮፻ ስድስት መቶ/ ሜማ በመሆኑ ከዛሬዎቹ ታላላቅ መርከቦች እንደሚወዳደር ግልጽ ነው። ዛሬ ያደጉ አገሮች አለን ብለው የሚኩራባቸው የንግድ መርከቦች ርዝመታቸው ፱፻ ሜማዎች ስፋታቸው ፩፻፭ ሜማ ተኩል ከፍታቸው ፩፻፭፱ ሜማዎች ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ፲፱ ክፍሎች ሲኖሯቸው አንድ ሽህ ሠራተኞች እሏቸው በጦርነትም ጊዜ ፲፩ ሽህ ወታደሮች ሊይዝ እንደሚችል ጣፋጭ ታሪክ በሚለው መጽሐፍ ተገልጿል ።

እግዚአብሔር ኖኅን ይህን ያህል ትልቅ መርከብ ሥራ ያለው ለምን ነበር ?

አንደኛው ማንም ሰው ለመዳን ቢፈልግ ቦታ እንዳለለት እንዲያውቅ

ሁለተኛ እግዚአብሔር ከአዕዋፍም ከእንስሳትም ሁሉ ዘር ለማስቀረት ስለፈለገ

ሶስተኛ ይህ መርከብ በዓለም ሆኖ የማያውቅ ሞገድና ነፋስ ስለሚሆን እንዲቋቋም ነበር ኖኅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ፕላኑን ነድፎ ሥራውን ጀመረ እንጨቱን አዘጋጀ መሠረቱንም ጣለ በመጀመሪያ ጊዜ ጐረቤቶቹ ልብ አላደረጉም ነበር ። በኋላ ግን ዓመታት እያለፉ ሥራው እያደገ ሲሔድ ኖኅ የሚሠራው ጐተራ ሳይሆን መርከብ መሆኑ ሲታወቅ መቀለድ ጀመሩ መሣቂያ መሣለቂያ አደረጉት ምክንያቱም ጥቅሙ አልታያቸውምና ነው ።

ይህ ትልቅ መርከብ ከኖኅና ከቤተሰቦቹ በቀር ማንም አጠገቡ ስለአልነበረ በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደተጠላ ለመገምገም አያዳግትም ።

ሽማግሌው ኖኅ ከ፭፻፳ ዓመታት በኋላ ጥፋት እንደሚመጣ ሲያስጠንቅቅ ቢኖርም የጊዜው ፍጻሜ እየተቃረበ ሲሔድ የጥፋት ምልክት ባለመታየቱ ተሣሥቶ ይሆን? የእግዚአብሔርን መልእክት ትርጉም አሳጥቶት ነውን? እንግዲህ ይህ ትልቅ መርከብ ያላገለግሎት ተገትር መቅረቱ ነው ? የሚል ጥርጣሬ አሳድሮ ነበር ።

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለማይቀር ኖኅ ዓለም በሙሉ ሊጠፋ ነው እንስሳት ሁሉ ወደመርከቡ የገቡ ስለዚህ ነው እያለ ይናገር ነበር ግን ሰሚ አልተገኘም እንዲያውም «ከእንስሳት ጋር ተዘግተህ ኑር» እያሉ በመቀለድ ወደቤታቸው ተመለሱ።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ለኖኅ እንዲህ አለው ግባ አንተ የቤትህም ሰዎች ሁሉ ወደመርከቡ ግቡ በዚህ ትውልድ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና ከሰባት ቀናት በኋላ ዝናብ በምድር ላይ አውርዳለሁና አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም የፈጠርሁትን ፍጥረት ሁሉ ከምድር አጠፋለሁ»

ምንጊዜም እግዚአብሔር ለሰዎች የንስሐ ዕድል ይሰጣቸዋል በዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎችም የንስሐ ጊዜ ተሰጥቷቸው ነበር ግን ሊጠቀሙበት አልቻሉም ።

የእግዚአብሔር መልእክት ሲተላለፍላቸው ጆሮአቸውን ደፈኑ ለመዳን ፍላጐት በጭራሽ አልነበራቸውም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል «ኖኅም ወደመርከቡ ገባ ልጆቹም ሚስቱም የልጆቹም ሚስቶች ከእርሱ ጋር ስለጥፋት ውኃ ከንጽሕ እንስሳ ንጹሕም ካልሆነው እንስሳ ከአእዋፍ በምድር ላይ ከሚንቀሳቀሰው ሁሉ ሁለት ሁለት ገቡ ።

እነዚህ ሁሉ ወደመርከቡ ከገቡ በኋላ ለሰባት ቀናት ያህል የጥፋት ውሃ ሲዘገይ የቀረ መስሎአቸው በኖኅ መሳቃቸውን ቀጠሉ በሰባተኛው ቀን ከባድ ደመና በሰማይ ላይ ከታየ በኋላ የዝናቡ ነጠብጣብ ማካፋት ጀመረ የዝናቡ ኃይል በየደቂቃው እየጨመረ ሄደ ከዝናቡ ኃይል የተነሣ ቤቶች ሁሉ እንደ ደጃ ሆኑ ጉርፋ በየመንገዱ ይደነፋ ጀመር ወንዞችና ጅረቶች ከአፍ እስከ ገደብ ሞሉ። ሰዎችም ወደከፍተኛ ቦታ መሯሯጥ ጀመሩ እንዲያው ደከሙ እንጂ ውሃ ተከተላቸው በምድር ላይም የነበረው ሁሉ ጠፋ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳና የሰማይ አዕዋፍ ድረስ ከምድር ጠፋ ኖኅም በመርከብ አብረውት ከነበሩት ጋር ብቻውን ቀረ ።

ታዲያ እግዚአብሔር ይህን አሰቃቂ የጥፋት ጊዜ ቢያመጣም መርከቢቱን በምሕረቱ ጠበቃት የወደፊቱ የዓለም ተስፋ ያረፈው በእነዚህ በመርከቢቱ ውስጥ በነበሩት ሰዎች ነበርና ነው

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በእርሱ ለአመኑ ቃሉን ለሚቀበሉ ቃልኪዳኑን ስለማያስቀር ኖኅና ቤተ ሰቦቹ በጠቅላላ በመርከቢቱ ውስጥ የነበሩት ከጥፋት ውሃ ዳኑ የጥፋት ውሃም በሁለተኛው ወር በ፲፻ በ፳፯ ቀን ከምድር ላይ ደረቀ ።

እግዚአብሔርም ለኖኅ «እንደገና ምድርን በውሃ አላጠፋትም» ሲል ቃልኪዳን ገባለት ዛሬም በዘመናችን መምህራንና አባቶች አንዳንድ ሰዎች ጥፋት ሲያጠፉ ሲያዩ ሲመክሯቸውና ሲያስተምሯቸው ከስሕተታቸው በመመለስና ንስሐ በመግባት ፈንታ የሚስቁና የሚሣለቁ አይታጡም።

ስለዚህ በኖኅ መርከብ የነበሩትን ሰዎች እግዚአብሔር ከጥፋት ውሃ እንዳዳናቸው ሁሉ እኛም በቤተ ክርስቲያን እየተገኘን የእግዚአብሔርን ቃል ብንሰማና ትእዛዙን ብንፈጽም ከማንኛውም ጥፋት እንደምንድን አያጠራጥርም ምክንያቱም የኖኅ መርከብ ምሳሌ አማናዊት ቤተ ክርስቲያን ናትና ።

ነቅዓ ጥበብ ወንድም





www.ethiopianorthodox.org

# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## ፩ የግሥ ቃላት አጠቃቀም ዘዴ

ለድርሰት ኃይልና ጥንካሬን ፣ ጥራትና ውበትን የሚሰጡት የግሥ ቃላት ናቸው ። ግሦች በማናቸውም ድርሰትና በንግግር ጥበብ ሁሉ እንደሁለገብ የቁልፍ መፍቻ ሆነው ያገለግላሉ ። የግሥ ቃላት የበዙበት ንግግር ልክ እንደ እሩምታ ተኩስ ብርቱ ንቅናቄና የጋለ ስሜት የሚፈጥር ይሆናል ። ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ሕይወት የሚሰጡትና ነፍስ የሚዘሩበት ግሦች ናቸው ።

ስለግሦችም አጠቃቀም ዘዴ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ጥሩ መመሪያ ነው ማለት ይቻላል ። ለምሳሌ በመዝ-፲፰ ፩—፱ ፤ ፩ ፣ ፩—፱ ፤ ሉቃ- ፲፭ ፣ ፫—፲ ያለውን ምልዓተ ግሥ መመርመሩ እንኳ ይበቃል ። ይኸውም በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ቋንቋዎች የልዩ ልዩ እትሞችን ስልት እያገናዘቡ ማጥናት ይጠቅማል ።

## ፪ ተሻጋሪ ግሥ ከማይሻገር ግሥ የሚበልጥበት መሠረታዊ ጠባይ

በቅዱሳት መጻሕፍት የቃላት አገባብ ብዙ ጊዜ ጠቃሚ መልእክት የሚተላለፍባቸው ሥዕላውያን የቅኔ ንግግር ታሪክና ምሳሌዎች ሁሉ ከተገለጡባቸው ቃላት አብዛኛዎቹ ተሻጋሪ ግሦች ናቸው ። ለምሳሌም ራዕዩን ጻፍ (ራይት ዘቢዥን የተሰኘ አንድ የእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ መመሪያ በገጽ ፲፬—፲፭ ካሠፈራቸው የሚከተለውን እንመልከት ፣— «በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ የአንጎላ ተማሪ አራት ያህል የአፍሪቃውያንን ታሪክና ምሳሌዎች ጥናት በመጥቀስ የምሳሌያዊ ንግግሮቹ ቁልፍ መሣሪያዎች ተሻጋሪ ግሦች መሆናቸውን ጠቁሟል እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

፩- የሚያገሣ አንበሳ አውሬ ለማደን አይችልም ፤

፪- የብዙ ወጥ ሠሪዎች ልፍለፋ ሩዝ አያበስልም ፤

፫- የገመዱን ጫፍ ይዘህ ብትከተል አህያህ ወደ ምትገኝበት ሥፍራ ያደርስሃል ፤

፬- አንድ ዓይና ሰው ሙሉ ዓይነ ስውር የሆነውን የአንድ ሌላሰው ሁኔታ እስካላየ ድረስ እግዚአብሔርን አያመሰግንም ። »

ሌላው አንድ ደቀ መዝሙር በግሪን ላንድ የሥነ ጽሑፍ ጥናት ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ስለቃላት አጠቃቀም ከጻፈው ጠንካራ ስሜት የሚከተለውን ጠቅሰናል ። «እንደ እኔ አመለካከት ቃላት ዓለምን መለወጥ ይችላሉ በአገባብና በሥነ ሥርዓት ከተጠቀሙባቸው ቃላት ከወርቅና ከአልማዝ የበለጠ ዋጋ አላቸው ። በማንኛውም ዓይነት ቋንቋ ይጻፍ እንደጥሩ መጽሐፍ ዘለዓለማዊ ኑዋሪነት ምንም ነገር በዓለም ላይ አይገኝም ። በተለይም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት ባሏቸው ውብ ቃላት ሁሉ ጊዜ አዲስ እንደሆኑ ለዘለዓለም ይኖራሉ » (ቴይላንድ ) ።

## የዓረፍተ ነገር አመሠራረትና የአሳብ አወቃቀር (ሎጂክ)

ሰው በዙሪያው ያሉትን ያካባቢ ነገሮች ሁኔታ ሲመረምር ሐሳቡን በምን ዓይነት ዘዴ እንደሚመራ አቅጣጫውን ሁሉ ማወቅ ያስፈልጋል ። ላቀደውም ነገር ሁሉ ትክክለኛውን መልክና ቅደም ተከተል መስጠት ይወዳል። ትክክለኛውንም መሥመር ተከትሎ ወደእውነት መድረስና አመለድረሱን ማመዛዘን የሚችለውም «ሎጂክ ተብሎ በሚጠራው የጥናት ንድፈ ሐሳብ ነው ሎጂክ በድርሰትም ሆነ በንግግር ጥበብ ውስጥ ዋና የተግባር መመሪያ ነው ። ይኸውም በሰው አእምሮ የሚቀነባበሩ ሐሳቦች ሁሉ በምን ዓይነት ዘዴ ቅደም ተከተል ይዘው መሰናዳት እንዳለባቸው የሚከተሉትም የተፈጥሮ ሕግ እንዳላቸውና በምን ዓይነት ሥነ ሥርዓት እንደሚከናወኑ ፤ እንዲሁም ስሕተት ላይ ለመውደቅ የሚያደርሱ ነገሮችና ምክንያቶችም ምን እንደሆኑና ከየት እንደመጡ ጠቅላላ ሁኔታዎችን መርምረንና ገምግመን የምንረዳበት የጥናት ክፍል ይኸው ሎጂክ የሚባለው የሥነ ጽሑፍ መመሪያ ንድፈ ሐሳብ ነው ።

ይህ በዚህ እንዳለ ማናቸውም ነገር የሚገለጥበት መንገድ ወይም መገኛውና መገናኛው ቋንቋው ነው ። ስለዚህም አንድ ዓይነት ሐሳብ መግለጥ በምንፈልግበት ጊዜ ተስማሚ የሆኑትን ውብ ቃላት መርጠን በመውሰድና ዓረፍተ ነገር በማበጀት የሰዋስውን ደንብ ሁሉ መከተል አለመከተላችንን ለይተን የምናውቅበትም የጥበብ ሚዛን ሎጂክ ነው ። ስለዚህም ሎጂክ በቋንቋና ከሰዋስው ጥናት ጋር ግንኙነት ያለው ነው።ለድርሰትም ሥራ ዋና ዋልታና ምሰሶ ነው ለማለት ያስደፍራል። ደራሲ የሚያምነው ሐሳብ ሁሉ በሎጂክ ካልተደገፈ በቀር ከዕብድ ልፍለፋ የተለየ ይዘት አይኖረውም ። የዚህንም ሁሉ ተግባራዊ ማስረጃ በሚከተለው እትም በምሳሌ እናቀርባለን ።

ቄስ መክብብ አጥናው ።



# ዜና ሊቃውንት

## መልአከ ሰላም እውነቱ

በጐጃም ክፍለ ሀገር «አባዛኸኝ» ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በ፲፰፻፹፰ ዓ-ም የተወለዱት መልአከ ሰላም እውነቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በልጅነት ዕድሜያቸው ያደጉት በአጐታቸው በፊታውራሪ ተድላ ፀሐዩ ቤት ነበር።

መልአከ ሰላም የመጀመሪያውን የንባብና የዳዊት ድጋም ትምህርታቸውን በዚያው በአጐታቸው ቤት እንዳሉ ከተማሩ በኋላ «ደቢት» ከነበሩትና በጣም ከታወቁት የመዝገብ ድጓ መምህር ከመሪጌታ ዓቢይ ኑርልኝ መዝገብ ድጓ በጠቅላላውም ጸዋትወ ዜማን ተምረዋል ።

ከዚህም በኋላ ወደ ላስታ ሔደው በቅኔ ሞያ ችሎታቸው በጣም ይደነቁ ከነበሩት ከአለቃ አባተ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው ከመማር ወደማስተማር የሚያደርሰውን ዕውቀት ገብይተዋል። ከዚያም ወደ ደብረታቦር አምርተው እጅግ የሚመሰገነውን የአለቃ ተክሌን ዝማሜ በአጠቃላይ አቋቋሙን በሚገባ አጥንተዋል ።

ከዚህም ሌላ ከተለያዩ መምህራን የመጻሕፍተ ሐዲሳትንና የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አደላድለው አውቀዋል ፣ ይልቁንም በፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ እጅግ ታዋቂና ስመ ጥር እንደነበሩ ይነገርላቸዋል ።

መልአከ ሰላም በትምህርት በምርምርና በአስተያየት በጣም ተወዳጅ ስለነበሩ መኖሪያቸው በራስ ቢትወደድ መንገሻ ቤት እንዲሆን ተደርጐ ነበር ። ራስ ቢትወደድ መንገሻ ቡሬ ሚካኤልን ሲደብሩም ለመልአከ ሰላም እውነቱ በዚሁ ደብር የሊቀ ጠበብትነት መዓርግ ሰጥተው ከቤተ ክርስቲያን በአገልግሎትና በማስተማር ፣ ከእሳቸውም በምክር እንዳይለዩ አድርገዋል ።

መልአከ ሰላም በራስ ቢትወደድ መንገሻ ዘንድ በባለሟልነት ይኖሩ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ በፍርድ አሰጣጥ በአስተዳደር ሥራ ለተበደሉ ባለጉዳዮችና ችግረኞች በማስታወስ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከሊቅነታቸውና ከፍ ካለው የአስተያየት ዝንባሌያቸው በላይ ተጨማሪ የሆነ ከፍተኛ ግምት ሊያሰጣቸው ችሏል ። ብለው የሚገመግሙ ብዙዎች መሆናቸው ተረጋግጧል ።

ራስ ቢትወደድ መንገሻም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ቀደም ብለው በቅርብ ያውቋቸው የነበሩት ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ደብረ ዘይት ተብላ ለምትጠራው ደብር አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ፈቅደው ስለማናቸውም ዓይነት ምክክር እንዳይለዩዋቸው አድርገው በከፍተኛ አስተያየትና ግምት ይመለከቱዋቸው ነበር ።

ግፈኛው ጠላት ከኢትዮጵያ ከተባረረም በኋላ በ፲፱፻፴፫ ዓ-ም መልአከ ገነት ተብለው የሞጣን አስተዳዳሪነት ተሾመው የተጣለባቸውን አላፊነት በተለመደው ትጋታቸው ሲያከናውኑ ከቆዩ በኋላ «መልአከ ሰላም» በሚያሰኝ መዓርግ ወደደምበጫ ደብር አስተዳዳሪነት እንዲዛወሩ ተደረገ ።

በ፲፱፻፴፯ ዓ-ም ስለሊቀ ጵጵስና ሹመት መብት ጉዳይ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስለተነሣው ከፍተኛ ክርክር ከየክፍላተ ሀገሩ ሁለት ሁለት ሊቃውንት በካህናትና በምእመናን እየተመረጡ ወደዋናው የኢትዮጵያ ከተማ አዲስ አበባ መጥተው በጉዳዩ እንዲመክሩበትና አሳብ ለአሳብ እንዲለዋወጡበት ሲደረግ በጐጃም ክፍለ ሀገር በኩል ከተመረጡት ሁለት ሊቃውንት አንደኛው መልአከ ሰላም እውነቱ ነበሩ ።

መልአከ ሰላም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጵጵስና፣ በጠቅላላውም ራሷን ችላ የሊቀ ጵጵስና መብት ይገባታል አይገባትም በሚለው መሠረታዊ ክርክር ላይ ለመነጋገር በተሰበሰበው ጉባኤ መካከል በየጊዜው ያቀርቡት የነበረው አሳብ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የተጠየቀውን የመንፈሳዊ መብት ተቅዋም ለማጠናከርና ፈር ለማስያዝ ቀጥ ያለውን የክርክርና የጥያቄ ጐዳና በር ከፍቷል የሚል ዜና በጊዜው በጉባኤው አካባቢ ከሚደርሰው ዜና ሊታወቅ ተችሎ ነበር ።

በመሠረቱ የሊቃውንቱ የክርክር መድረክ የተከፈተው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን «ዋና ቀኖና» «የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ሊቀ ጳጳሳትን አይሹሙ» ይላል ተብሎ በፍጹም ሐሰት ላይ ተመሥርቶ በቀረበው ጥቅስ ስለነበረ እንደኢትዮጵያ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ለምሳሌ በሶርያ፣በቁጥስንጥንያና በአንጾኪያ የፍትሐ ነገሥቱ ድንጋጌየማይገኝና ግብጾች ለጥቅማቸው ሲሉ ራሳቸው በራሳቸው የጻፉት መሆኑን ፣ ከዚህም ሌላ ሦስቱ መቶ አሥራስምንቱ ሊቃውንት በኒቅያ የተሰበሰቡት እንደኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፫፻፲፰ ዓ-ም ሲሆን ፣ ኢትዮጵያ በከሣቴ ብርሃን ሰላማ አማካይነት ክርስትናን የተቀበለችው ከ፫፻፴ ዓ-ምበኋላ በመሆኑ ክርስትናን ከመቀበሏ በፊት ሊቀጳጳስ ከተወላጇ እንዳትሾም ሕግ ተሠራባት ማለት የውሸት ውሸት ነው ባሚለው ኃይለ ቃል ላይ ስለነበረ በፍትሐ ነገሥቱ መምህር ለመልአከ ሰላም እውነቱ ለዚህ ዋስትና ለሌለው የጭፍን ክርክር አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የተመቸ ሆነላቸውና ይኸንኑ ክርክር ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው እየተወከሉ ከመጡት መልእክተኞች ለመከራከርና በቀዋሚነትም በጊዜው ተቋቁሞ ከነበረው የዓቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ቋሚ አባል ሆኖ



www.ethiopianorthodox.org

ለመሥራት መልካም የሆነ ዕድል አስገ ኙላቸው ።

ጠላት ኢትዮጵያን ከለቀቀ ወዲህ በዚ ያው በጐጃም ክፍለ ሀገር በተሾሙ በት ደብር ስለአጋጠማቸው የአስተ ዳደር መዛባት የቤተ ክርስቲያንን መ ብትና ክብር ለማስጠበቅ ሲሉ ዝርዝር ሁኔታውን ለመንግሥት አመልክተው ከሁለት ሦስት ጊዜ ከአዲስ አበባ ወደ ክፍለ ሀገሩ ደብዳቤ ይዘው ቢሔዱ የተ ሰጠው ትእዛዝ ተከብሮ ባለመፈጸሙ ከፍ ያለ ብስጭት አጋጠማቸው ።

በዚህም ጊዜ በቅኔ ሞያቸው እጅግ የተመሰገኑ ሊቅ ነበሩና ይኸንኑ የደረ ሰባቸውን ችግር አስመልክተው በ፲፬ ፻፴፰ ዓ-ም ለብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮ ርጊስ (በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስ ልዮስ) ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መወ ድስ ቅኔ አበረከቱ ።

ንቃሕ ሊቅ ገብረ ጊዮርጊስ ፣ አም ጣነ ተሐውከት ብነ ቤተ መቅደስነ ባሕር እስከ አሐዘተ ትሠጠም ሕገ አ ቡከ ሐመር ።

መገሥጽ ነፋሳተ በኃይለ አድኅኖ ዘያዕቆብ በትር

እስመ ዘልፈ ይጸርሁ ፣ ወይወውዑ ኀቤከ አድባር ወአውግር

ኢክህለሂ ለሕግነ አግዕድዎቶ በም ድር ።

መሐፒል ቃለ ንጉሥ እምኩሉ ዘይ ከብር

ቤተ ክርስቲያን ተሐጊባ እስመ ገብ ዓት ዲበ ጸብር

(አማርኛ) የአባቶችህ ሕግ መርከብ እስክትሰጥም ድረስ ባሕር ቤተ መቅደ ሳችን ታውካብናለችና ሊቅ ገብረ ጊዮ ርጊስ ንቃ ፣ አድባራቱም ወደ አንተ ይጮሃሉና የያዕቆብ በትር በሆነው በድኅነት ኃይል ነፋሳትን ገሥፅ

ከሁሉ የሚከበር የመንግሥት ቃል ሳሙናም ሕጋችንን ሊያነጣው (ሊያ ጸዳው) አልቻለም ፣ ቤተ ክርስቲያን ታጥባ ከጭቃ ገብታለችና የሚል ነው

መልአከ ሰላም ይኸንን ቅኔ ሊቀኙ የቻሉት በምን ዓይነት ብስጭት እንደ ሆነ ወዲያውኑ ዘርዝረው አስረድተ ዋል ።

ይሁን እንጂ ይህ ቅኔያቸው በዘመኑ በነበሩት ከፍተኞች ባለሥልጣኖች ዘንድ ተሰምቶ ተወቀሱበት ፣ እንዲያ ውም ከእሥር ቤት ገቡበት እንጂ ስለ ተሾሙበት ደብር አስተዳደር ያቀረ ቡትን አቤቱታ ፈር ሊያስይዝላቸውና ትክክለኛውን የፍትሕ አቅጣጫ ሊቀ ይስላቸው አልቻለም ።

መልአከሰላም ከላይ ከተዘረዘረው ከትምህርት ፣ ከአስተዳደርና ከማስረ ዳት ችሎታቸውም ሌላ ብሔራዊውን ባህልና ታሪክ ጠንቅቀው ያወቁ ስለ ነበረ በዚህ ረገድ ለሚቀርብላቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች የሚያቀርቡት መልስ እጅግ አጥጋቢ እንደነበረ ይነገርላቸ ዋል ።

ትምህርታቸውንም ሆነ የተፈጥሮ ዕውቀታቸውን እንዲሁም የረጅም ጊዜ ልምዳቸውን በዚህና በመሳሰለው ም ዓይነት ሁሉ ተግባራዊ ሲያደርጉ የነበሩት መልአከ ሰላም እውነቱ የሰው ልጆችን ሥጋዊ ሕይወት በሚ ያጠምደውና በማይቀረው ሞት ተጠ ርተው በ፲፱፻፶፩ ዓ-ም በነሐሴ ወር ከሥጋዊ ሕይወት ወደ ነፍሳዊ ሕይወት ተላለፉና ቀብራቸው በዚያው በሚያ ስተዳድሩት ደብር በደምበጫ ተፈጸመ

ከአለቃ አምደ ጽዮን ተሰማ

## ሥርዓተ ገዳም

ግላዊ ጥሪት ሳይፈልጉ ያላቸውን ሁሉ ለማኅበሩ ሰጥተው ማኅበሩን እያ ገለገሉና በማኅበሩ እየተገለገሉ ለመ ኖር ፈቅደውና በምናኔ ተሰባስበው በአንድነት የሚኖሩ መናንያን ማኅ በር ገዳም ይባላል ። ይህ ገዳማዊ ሥር ዓተ ኑሮ የተመሠረተው በሦስተኛው ምእት ዓመት በእነ አባ እንጦንስና መቃርስ ነው ።

መናንያነ ዓለም (መነኮሳት) እየበዙ ሲመጡና ገዳማዊ ሥርዓተ ኑሮ እየተ ስፋፋ ሲሄድ ማኅበሩ የሚመራበት ሕግ ፤ እያንዳንዱም የማኅበር አባል እንዴት ሆኖ መኖር እንደሚገባው የሚያመለክት መመሪያ አስፈለገ ። ስለሆነም ከማኅበሩ መካከል የበቁና የነቁ አበው በርከት ያሉ ድርሳናትን ተግሣጻትንና ቀኖናትን ጽፈውና አስ ተምረው አልፈዋል ። ራእይ አይተ ዋል መጻእያትንም ተናግረዋል ።

ለምሳሌ ፊልክስዩስ የመነኮሳትን ገድልና የምንኩስናን ታሪክ ፤ አረጋዊ መንፈሳዊ የመነኮሳትን ጸጋና ማዕርግ ማር ይስሐቅ የመነኮሳትን ግብርና ጠባይ የሚያጋጥማቸውን ጾርና ድል የሚያደርጉበትን መንፈሳዊ ጥበብ ጽፈዋል አስተምረዋል ።

አባ ጳውሊም ከአባ እንጦንስ ቀጥ ለው የሚነሱ ንጹሐንና ጻድቃን መነ ኮሳትን በዕዕድዋን አርጋብ ተመስ ለው ፤ ፪ኛ በመካከለኛው ዘመን የሚ ነሱ መነኮሳት ደግሞ አንድ ጊዜ ወደ ምናኔ በሌላ ጊዜ፤ወደ ግብረ ዓለም በማ ለት ጽድቅንም ኃጢአትንም የሚሠሩ ስለሆነ በአምሳለ አርጋብ ኰሳኵሳን በክንፋቸው ጥቁር በተቀላቀለባቸው አርጋብ ተመስለው ፤ ፫ኛ በፍጻሜ ዘመን የሚነሱ መነኮሳት ግን አርጋብ ወይም ርግቦች ሆነው ሳሉ እንደ ቁራ የጠቆሩ ሆነው ታይተውታል ። ስለሆ ነም በኋላ ዘመን የሚነሱ መነኮሳት ሹመት ፈላጊዎች ፤ ገንዘብ ወዳጆች ከመኳንንትና ከመሳፍንት ጋር መብላ ትንና መጠጣትን አዘውታሪዎች ከደ ገኛው ሕገ ምንኩስና የራቁና ከጽድቅ መንገድ የተለዩ ኃጥአን ይሆናሉ በማ ለት ለአባ እንጦንስ አስረድቶአል ።

በመሠረቱ « ምንኩስና የመሲሐ ዊት ሕግ (የሕገ ወንጌል) ጥበብ ናት መነኮሳትም ምድራውያን መላእክት ሰማያውያን ሰዎች ናቸው ። ከዚህ ዓለም ጥሪት ተለይተው ፈቃደ ሥጋን



ትተው — በሥራ ሁሉ ክርስቶስንና ሐዋርያትን በመምሰላቸው ብፁዓን ናቸው» ተብሎ በአንቀጸ መነኮሳት ተጽፎአል ።

መናኝ (መነኩሴ) የግል ጥሪት ቁሪት የሌለው ፤ ከዓለማዊ ግብር የተለየ የዓለምን ፈቃድና ፍቅረ ንዋይን አስ ወግዶ ከሥጋ ዘመዶቹ ተለይቶ ፤ በገ

አል ። መነኩሴ «ምንም ገንዘብ አያ ጠራቅም የላመ የጣመ አይብላ —» የሚል ሥርዓት አለ ። ፍትሕ መንፈ ሳዊ አንቀጽ ፲ ፣ ፫፻፸፱ ።

በዚህ ሁኔታ ሥርዓተ ገዳምን ጠብ ቀው ሕገ ምንኩስናን አክብረው በጾም በጸሎትና በትሩፋት ተወስነው ድኩ ማን ሥጋን በትሩፋት ድኩማን ነፍስን



አባ እንጦንስና አባ ጳውሊ ።

ዳም ለመኖር የወሰነ ፤ በጾምና በጸሎት ጽሙድ የሆነ ፤ ለሥራ የሚተጋ እግዚ አብሔርን ለማሰብ መጻሕፍትን በማ ንበብ ትርጓሚያቸውን ለማወቅ የሚ ጥር መሆን እንዳለበት በፍትሐ መን ፈሳዊ በአሥረኛው አንቀጽ ተገልጦ

በትምህርት ከሚረዱት መነኮሳት መካ ከል ቤተ ክርስቲያን እየመረጠች፤ከኤ ጲስ ቆጶሳት እስከ ፓትርያርክነት በመ ሾም ምእመናንን እንዲመሩ ፤ እንዲያ ስተምሩና እንዲጠብቁ ታደርጋለች ። ይኸውም በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ ፣ ፹፱ እና ፹፱ ላይ «በየቦታው ላሉ አብያተ ክርስቲያናት ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የሚሾመው ጠባዩ ያለ ነውርና ያለ በደል ይሁን—፤ከሰው ሁሉ በደል የነጻና ሥልጣነ ክህነት ካላቸው ከመነኮሳት ወይም የሚያስመሰግን ሥራ ካለው ወገን የሆነ መነኩሴ ይሁን ተብሎ በተወሰነው መሠረት

በትሩፋቱ በንጽሕናውና በደግነቱ ምእመናን ሲመሰክሩለት ቤተ ክርስ ቲያን ከአለበት ፈልጋ በመጥራት ከም ትሾመው በቀር መናንያነ ዓለም መነ ኮሳት ከዓለማዊ ግብርና ሹመት መራቅ እንደሚገባቸው የምንኩስና ሥርዓት ያስረዳል ። የሥራ አመራራቸው ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ፤ ገድላቸው ትሩ ፋታቸውና ትምህርታቸው ለምእመ ናን አንድነት ለሃይማኖት ጽንዓት ይሆ ናል ተብሎ ሲመሰክርላቸውና ሲታ መንባቸው ከያሉበት ገዳም እየተፈ ለጉ በውድም ሆነ በግድ እየተሾሙ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውንና አመ ራራቸውን ለቤተ ክርስቲያን እንዲያ በረክቱ ሥርዓቱ ይፈቅዳል ። «መራ ጮች የዚች ሹመት ሥርዓት የምትገ ኝባቸውን ብዙ ሰዎች (መነኮሳት ) ቢያገኙ በሥርዓትዋ ከእነርሱ ፍጹም የሆነውን ይምረጡ ። የተመረጠውም ሹመቱን አልፈልግም ቢል ሌላውን ይምረጡ ሌላው በቂ ሆኖ ባይገኝ ግን የፈተኛውን ለሹመቱ ተገቢ ሁኖ የተ ገኘውን ሊተውት አይገባም በግድ ይሹሙት» ተብሎ በፍትሐ መንፈ ሳዊ አንቀጽ ፭ ፣ ቁ ፳፫ ታዝዞአል ።

ከዚህ በተረፈ ግን መናንያነ ዓለም መነኮሳት ከሥጋዊ ሹመት መራቅ ይቅርና ከመንፈሳዊ ሹመትም እንኳን መለየት እንደሚኖርባቸውና በልመና፣ በደጅ ጥናትና አማላጅ መሾም እንደ ማይገባቸው ሥርዓቱ እንዲህ ይላል። «መናኝ የክህነትና የሹመትሥራ መው ደድ አይገባውም ። የሹመት ፍቅር የ— በሽታ ነው በዚህ በሽታ የወደቀ ሰው ክህናትና ሹማምንት ሊሆኑ በሚ ገባቸው ሰዎች ላይ ቀናተኛ ይሆናል። ሰው ጠቅሶ ያነሣሣባቸዋል ። በእነርሱ ሹመት ይተካ ዘንድ ሞታቸውን ይወ



www.ethiopianorthodox.org

ድጳል ። ሹመቱም ባልሆነለት ጊዜ በእርሱና በእነርሱ መካከል ችግር ይፈጥራል ። ስለዚህ ከዚህ መጥፎ ፈቃድ ይራቅ --- መናኝ (መነኩሴ) በፍጹም ልቡ ከወላጆቹ ከዘመዶቹና ከሕዝባውያን ወገኖቹ መለየት ይገባዋል ። ሙት ከሕያዋን እንደሚለይ ሁሉ መነኩሴ ከሰብአ ዓለም መለየት አለበት ፍ-መ-አ ፲ ፡ ፫፻፹፭

በኢትዮጵያ ቀደም ባሉት ዓመታት ብዙ የአንድነት ገዳማት ነበሩ አሁንም አሉ በነዚህም ገዳማት ሥርዓተ ገዳምን አጽንተው ሕገ መንኩስናን አክብረው የዚህን ዓለም ጥሪት ትተው ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ለማኅበሩ አላማ አውለው በትሩፋታቸውና በተግባረ እድ ውጤታቸው ገዳማቱንና አብያተ ክርስቲያናቱን አስጊጠው ያለፉ ብዙ ቅዱሳን መነኮሳት ለመኖራቸው ዛሬ በየገዳማቱና በየቤተ ክርስቲያኑ በቅርስነትና በአገልግሎት ላይ የሚታዩት ቅርጻቅርጽ ፤ ሥዕላትና የብራና መጻሕፍት ዕውነተኞች ምስክሮች ናቸው ።

ዛሬም ያለፉትን ቅዱሳን አበው ፈለግ የሚከተሉ ብዙ ዕውነተኞች መነኮሳት አሉ ። እነርሱም እንደ ቀደሙት አባቶቻቸው የገቡበትን የምንኩስና ቃል ኪዳን አጽንተው ሕገ ምንኩስናን አክብረው ሥርዓተ ገዳምን ጠብቀው በአንድነት የሚኖሩና በምእመናን ምስክርነት በቤተ ክርስቲያን ጥሪ በከፍተኛ መንፈሳዊ ኃላፊነት ተመድበው መንፈሳዊአመራራቸውንና አገልግሎታቸውን ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክቱት ብፁዓን አባቶች ድኩማን ሕሊናን በትምህርት ድኩማን ሥጋን በትሩፋት ይረዳሉ ያጽናሉ ።

እርግጥ አንዳንዶቹ ምንኩስና የዚህን ዓለም የኑሮ ሸክም የሚያቃልልና ሥጋዊ ብልጽግናን የሚያስገኝ እየመሰላቸው አመክሮአቸውን ሳይፈጽሙ ሥርዓቱን ሳይረዱ ይመነኩሳሉ። ግን የሚፈልጉትን ሥጋዊ ብልጽግና በምንኩስና የማያገኙ መሆናቸውን ሲያውቁ ከዕውነተኛው ፍኖተ ምንኩስና ሸግለል (ገለል) የሚሉም ጥቂቶች አይደሉም ። ከዚህም የተነሣ በአንዳንድ ኢመናንያን ስመ መነኮሳት ምክንያት ደገኛው የእነ አባ እንጦንስ አላማና ቆብ እንደማታለያ እየተገመተ ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ባሕታውያንና መነኮሳት ነን ባዮች ቀን በቆብ ማታ በ--- ስለሚታዩ ነው ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ጥንቃቄ ልታደርግበት የሚገባ ጉዳይ አለ ። ይኸውም ፩ኛ/ ወደ ምንኩስና ዓለም የሚመጡትን ካህናት ቀመስ ሰዎች ከማመንኮስ በፊት በምን ምክንያት ለመመንኮስ እንደፈለጉ በሚገባ መመርመርና ማጥናት ።

፪ኛ በእውነተኛ ምናኔ የመጡ መሆናቸው ከታመነ ወደታወቁ ገዳማት ሂደው አበው መነኮሳትን እየረዱና ከአበው መነኮሳት እየተማሩ የአመክሮ ጊዜአቸውን እንዲፈጽሙ ማድረግና ከዚያ በኋላ ማንነታቸው ሲታወቅ ማመንኮስ ።

፫ኛ/ በዕድሜና በአእምሮ የበሰለ የገባውን የምንኩስና ቃል ኪዳን አጥፎ ወደ ኋላ የማይመለስ መሆኑን ሳያረጋግጡ አለማመንኮስ ከመነኮሰም በኋላ ለሥራ ወይም ለትምህርት ፈልጋ ቤተ ክርስቲያን ካልጠራችው በቀር በመነኮሰበት ገዳም ጸንቶ እንዲኖር እንጂ ከገዳም ወጥቶ ወይም በዓቱን ትቶ ወደ ከተማ እንዳይገባ በጥብቅ መከልከል። በራሱ ፈቃድ ብቻ ከገዳሙ ወጥቶ ወደ ከተማ ቢገባ ግን ቤተ ክርስቲያን በሕዝባዊ ደረጃ እንጂ በምንኩስና ደረጃ የማትቀበለው መሆኑን ማስታወቅ ነው ።

«መነኩሴ የምንኩስናውን ሕግ ንቆ ከገዳሙ ቢወጣ ፡ በዚያ ይኖር ዘንድ ወደ ከተማና ወደ ገጠር ቢሄድ በዚያ በሚኖሩ ሕዝባውያን መዓርግ ይኑር በሕዝባውያን አምሳል እንጂ በመነኮሳት አምሳል እንደ መነኮሳት ይኖር ዘንድ አይገባውም እርሱ የምንኩስናውን አርአያ መከተል ባይችል በመነኮሳቱ ሁሉ ላይ ሐሜትን ያመጣባቸዋል ከፉ ስምም ያወጣላቸዋል» ተብሎ በአንቀጸ መነኮሳት ፲ ፡ ፬፻፳ ተወስኖ አል ። ይህ ውሳኔ በሥራ ቢተረጐም አሁን በአንዳንድ ስመ ባሕታውያንና ስመ መነኮሳት ላይ የሚታየውና የሚሰማው አሳፋሪ ድርጊት ይወገዳል ። «ነገ ግሸን ማርያም ከዚያም ላሊበላ እንሄዳለንና ስእለታችሁን እናድርስላችሁ» በማለት በየቤተ ክርስቲያኑ የምእመናን ገንዘብ ከሰበሰቡ በኋላ ለራሳቸ ውጥቅ ም የሚያውሉ ባሕታውያንመሰል ሰዎች አታላይነት ይታረማል ።እነዚህና የመሳሰሉት ጉድለቶች ሲታረሙሕገ መንኩስና ከተመልካቾች ትችትና ሽሙጥ ይድናል ። ሥርዓተ ገዳም ይጸናል ዕውነተኞች መነኮሳትም ምድራውያን መላእክት ሰማያውያን ሰዎችመሆናቸው ይታወቃል ምንኩስናም ሕግ መሢሐዊት መሆንዋ የጐላ የተረዳ ይሆናል ።

ራደ አስረስ

# በሕፃናት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ በሽታዎች

የሕፃንነት ጊዜ ከጽንስ ጀምሮ በአካልም ሆነ በዕድሜ በሰል እስኪሉ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል ። ስለሆነም እናትየዋ በእርግዝናዋ ወራት ጤናማ ካልሆነች የተመጣጠነ ምግብም ካላገኘች የሕፃኑ ጤንነት ሊቃወስ ይችላል ። ከተወለዱም በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች በበሽታ ሊጠቁና ጉዳት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ ። በሀገራችን ውስጥ ብዙውን ጊዜ ሕፃናት በበሽታ እንዲሰቃዩ ከሚያደርጋቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ እናቶች ስለ ሕፃናት ጠቅላላ አያያዝ ጥንቃቄና አመጋገብ ዘዴዎችን ጠንቅቀው ባለማወቃቸው የተነሳ ነው ። በሕፃናት ላይ ከሚደርሱት ዋና ዋና በሽታዎች ተላላፊ በሽታና የምግብ እጥረት ናቸው ።



እንደሚታወቀው ሕፃናት በቀላሉ በበሽታ የሚጠቁ ናቸው ። አንድ ሕፃን ፍላጐቱንና ስሜቱን ለመግለጽ የማይችል እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ወላጅ ሕፃኑ ጤነኛ ጠንካራና ደስተኛ ሆኖ እንዲያድግ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ጤነኛ ሕፃን ጤነኛ ሕዝብን ያፈራል አንድ ሀገር ሊያድግና ሊበለጽግ የሚችለው ጤነኛ ሕዝብ ሲኖረው ብቻ ነው ።

ከላይ እንደተገለጸው አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናት የሚታመሙት ወላጆቻቸው የጤና አጠባበቅና የበሽታን መከላከያ ዘዴዎች እንዲሁም ደግሞ ለሕፃናት የሚያስፈልጉትን ምግቦች ባለመመገባቸው የተነሳ ነው አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩትም ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች በሆኑት ሕፃናት ሃምሳ በመቶ የምግብ እጥረት እንዳለባቸው ታውቋል ።

ለሕፃናት ጤና ጠንቅ ከሆኑት አንዱ ዋናው ምክንያት ደግሞ በከተማ የሚኖሩ ሴቶች ጡት ማጥባትን እንደነውር እየቆጠሩ ሕፃኑ የሚበቃ የእናት ጡት ወተት ሳያገኝ ቶሎ ብለው ጡጦ ያስጀምሩታል ። በዚህም ጊዜ የቀጠነና ያልተመጣጠነ እንዲያውም ጡጦው በንጽሕና ስለማይያዝ በጡጦው ውስጥ ጐጅ የሆኑ ሕዋሳት (ጀርሞች ይከማቹና በሕፃኑ ላይ የተቅማጥና ትውከት በሽታ ያመጡበታል ።

በታመመ ጊዜም ወደ ሐኪም ቤት በመውሰድ ፋንታ ወደ ወጌሻ ወይም ጠንቋይና ባለውቃቢ ዘንድ በመውሰድ በሕፃኑ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጡ ድርጊቶች ለምሳሌ እንደ እንጥል መቁረጥ ግግ ማውጣት የመሳሰሉ ድርጊቶች ይበናወናሉ ። ቢያዘው በሽታ ላይ እንዲያውም ሌላ ተጨማሪ በሽታ ይዞ ይመለሳል ።

የእናት ጡት ወተት ለሕፃናት ተስማሚና ለሰውነታቸውም ተገቢ የሆኑትን የምግብ ዓይነቶች በሙሉ የያዘ የተመጣጠነ ምግብ በመሆኑ የጡት ወተት የሚመገቡ ሕፃናት ብዙውን ጊዜ የተቅማጥና የተውከት ሕመም አያጠቃቸውም ። የጡት ወተት ማሞቅ ማቀዝቀዝ ካለማስፈለጉም በላይ ለሕፃናት ተመጣጥኖ የተዘጋጀ ነው ። የእናት ጡት ወተት የገንዘብ ወጪ የለበትም ፤ ትርፍ ሥራም አይጠይቅም ። ንጽሕናን ከመጠበቅ በስተቀር

ኩብዙ እናቶች እንደሚሰማው ልጆቻቸውን ጡት የማያጠቡበት ምክንያት ጡታቸው ስለደረቀ ወይም ወተት ስለሌለው ነው የሚል ነው ። ይሁን እንጂ መገንዘብ ያለባቸው ሕፃኑ በጠባቂ ጡታቸው እያጋተና ወተት እየተካ መሔዱንና ካልጠባው ግን ጨርሶ የሚደርቅ መሆኑን ነው ። አንድ ሕፃን ትንሽም እንኳ ቢሆን በየቀኑ የጡት ወተት ቢያገኝ ለጤናው እጅግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ።

የእናት ጡት ወተት ያላገኘ ሕፃን በበሽታ ይማቅቃል ፤ ሰውነቱም እየደከመ ይሔዳል ። ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት የዱቄት ወይም የላም ወተትን አዘጋጅቶ በጡጦ መስጠት ዘጣም ብዙ ጥንቃቄና ንጽሕና ስለሚጠይቅ ነው ። አስፈላጊው ጥንቃቄ ለብዙዎቹ እናቶች አዳጋች ስለሆነ ጀርም የሞላበት ከዚያውም በተገቢው መንገድ ያልቀጠነ ወተት ይመገባል። በዚህም ምክንያት ተቅማጡና ትውከቱ እየተደጋገመ ስለሚይዘው ወደ አሰቃቂ ሁኔታ ይመራዋል ።

ሕፃናት ባለቀሱ ቁጥር እርቧቸው ነው ብሎ በማሰብ በየጊዜው ጡት ማጉረስ በተለይ በሀገራችን የተለመደ ነው ። እንዲያውም ብዙ እናቶች ሕፃናትን ዝም ለማሰኘት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው ። ይህ አድራጐት የተሳሳተና ጐጂ በመሆኑ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ። ይኸውም የሆድ መታወክና ጠባየ ብልሹነትን ሊያስከትል ስለሚችል ነው ።

ሕፃናት የሚያለቅሱት ከረሃብ ብቻ ሳይሆን ከብርድ ፣ ከሙቀት ፣ ከሽንት ጨርቅ መርጠብ ፣ ከሆድ ቁርጠትና ከሌላም ሕመሞች ሊሆን ስለሚችል ባለቀሰ ቁጥር ማጥባት በተለይ የቁርጠቱን ሕመም ሊያባብሰው ስለሚችል ያለቀሰበትን ምክንያት ተረድቶ መፍትሔ መፈለግ ነው ።

ሕፃናት የሚመገቡበትን ጊዜ ለይቶ ብየሦስትና አራት ሰዓት መመገብ በቂ ነው ። እንኳንስ ጨጓራቸው ገና ያልደረጀ ሕፃናት ይቅርና አዋቂ ሰውም እንኳ ጊዜ ሳይለይ ቀኑን ሙሉ ሲበላና ሲጠጣ ቢውል በቁንጣን ሊሰቃይ እንደሚችል የታወቀ ነው።

አንድ ሕፃን የላም ወተት በንጹሕ ጡጦ ቢመገብ እንኳ ጡት ከሚጠባው ሕፃን እኩል ጤነኛ ሊሆን አይችልም ይኸውም የእናት ጡት ወተት የሆድ ሕመምንና ሌሎችንም ልዩ ልዩ በሽታዎች የመከላከል ኃይል ስላለው ነው በጨቅላነታቸው ጊዜ የላም ወተት የሚመገቡ ሕፃናት የአለርጂ ሕመም ያጠቃቸዋል ።

የእናት ጡት ወተት ለሕፃኑ ጨጓራ ተስማሚ ከመሆኑም በላይ ሕፃኑ ሚዛን እንዲጨምርና ሰውነቱም በሚገባ እንዲዳብር ያደርጋል ። ጡት ማጥባት እናትና ልጁን ስለሚያቀራርብ ለሁለቱም በተለይም ለሕፃኑ እንክብካቤን የመንፈስ ደስታንና የፍቅር ስሚትን እንዲያገኝ ያደርገዋል ፤ ጤናማና ደስተኛም ሆኖ እንዲያድግ ያደርገዋል ።

የእናት ጡት ወተት ለሕፃናት ጠቃሚ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጾ ጠቃሚነቱ ለሕፃኑ ብቻ ሳይሆን ለእናትም ጭምር ነው ። ይኸውም ጡት ማጥባት እርግዝናን ለመከላከል የሚረዳ መሆኑ ስለሚታመንበት ሳይፈልጉ በየዓመቱ ከመውለድ ሊያዘገይላቸው ይችላል ፤ በሌላ በኩል ደግ የጡት ካንሰር (ነቀርሳ) እንዳይዝ የሚከላከል ለመሆኑ አንዳንድ ጥናቶች ያስረዳሉ ።

የእናት ጡት ወተት ጠቃሚነቱ



www.ethiopianorthodox.org

እየተረጋገጠና እየታመነበት ስለሔደ በአውሮፓና በሌሎችም በብዙ በው ሰጠኑ አገሮች እናቶች ከጡጦ ማጥ ባት ወደ ጡት ማጥባት እየተመለሱ ነው ።

ሕፃኑ አራት ወር እስኪሞላው ድረስ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ከእናቱ ጡት ያገኛል ፥ እያደገ ሲሔድ ግን የም ግብ ፍላጐቱን ስለሚጨምር ሌላ ተጨማሪ ምግብ ያስፈልገዋል ። አን ንድ እናቶች ጭራሽ እናጠባም ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ዓመት እስኪሞ ላው ከጡት በስተቀር ሌላ ምግብ የማ ይሰጡ አሉ ። በዚህ ጊዜ የሚያድገው ብቻ ሳይሆን የአእምሮን መጐልመስ ጭምር ነው ። ስለዚህ ቢያንስ ዓመት እስኪሞላው ድረስ ከተጨማሪ ምግብ ጋር ጡት ማጥባት እጅግ ጠቃሚ ነው የሚሰጠው ተጨማሪ ምግብም ለአዋ ቂዎች ከተዘጋጀው ባይሆን ጥሩ ነው ምክንያቱም የአዋቂዎች ምግብ በር በሬና ቅመማ ቅመም ስለሚበዛበት ለሕፃኑ የሆድ መታወክ ሊያመጣበት ስለሚችል ነው ። ተጨማሪ ምግብን ለመስጠት ቀስ በቀስ ማለማመድ ይጠ ቅማል ። ጨጓራው ያልለመደው ምግብ ባንድ ጊዜ በብዛት መመገብ የሆድ ሕመምንና መታወክን ከማስ ውሱ ሁለት ዋና ዋና በሽታዎች ውስጥ አንዱን ማለትም የምግብ እጥረት በሽታን በሚመለከት ከነምፍትሔው አይተናል ። ስለአንደኛው ደግሞ በሌላ ክፍል ለማየት እንሞክራለን ።

በመጨረሻም ለወላጆች የምሰጠው ሐሳብ ቢኖር እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት ለሕይወቱና ለኑ ሮው የሚያስፈልገውን አስቀድሞ እንደፈጠረ ለሕፃናትም ከላይ እንደ እንደተመለከትነው ተወዳዳሪ የማይ ገኝለትን ምግብ ዘጥቦቡ አዘጋጅቷል ስለዚህ ይህን ስጦታ በሚገባ በመጠ ቀም የልጆቻችሁን ጤንነት ብትጠ



በጥንቃቄ የተያዘ ሕፃን



በምግብ አጠባበቅ ጉድለት በተቀማጥ በሽታ የታመመ ሕፃን

ሰውነቱ በቂ ምግብ ስለማያገኝ የም ግብ እጥረት ሕመም (ማራስመስ) የተ ባለው በሽታ ይይዘዋል ። የምግብ እጥ ረት የሚጐዳው የሰውነትን መዳበር ከተሉም በላይ ሕፃኑ ያንን ምግብ ጠ ልቶት እንዳይቀር ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

እንግዲህ የሕፃናት ጤና ከሚያቃ ብቁ ልጆች የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ናቸው የሚለውን ቃል እያስ ታወሳችሁ ልታመሰግኑ ትችላላችሁ። ተማሪ ነርስ የሽአረግ ሥርጋዊ



ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው ፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ ማቴ- ፲፱-፭

ሚስት በገዛ ሥጋዋ ሥልጣን የላትም ሥልጣን የባሏ ነው እንጂ ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ሥልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ ፤ ፩ኛ/ ቆሮ ፯-፬

ብልሃተኛ ሴት ቤትዋን ትሠራለች ሰነፍ ሴት ግን በእጅዋ ታፈርሰዋለች ፤ መ/ምሳሌ ፲፬-፩

መልካሚቱን ሴት ማን ያገኛታል ፤ ከክበር ዕንቁ ሁሉ ይልቅ ዋጋዋ ፤ ይበልጣል መ/ መክብብ ፴፩-፲



ዲያቆን ለይኩን ብርሃኑ እና ወይዘሪት ንብረት አበበ ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋ ወደሙ በመሠረቱበት ወቅት ፤

ለእያንዳንዱ ወንድ ለራሱ ሚስት ትኑረው ፤ ለእያንዳንዲቱ ሴትም ለራሷ ባል ይኑራት ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት እንዲሁም ሚስት ለባሏ የሚገባውን ታድርግለት ። ፩ኛ/ ቆሮ ፯-፱

መጋባት በሁሉም ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ነው ፤ ዕብራውያን ፲፫-፬



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ የግዕዝ ትምህርት

## ትምህርት ፩

| ሥርዐተ ተናብቦ | የተናባቢ ሥርዓት |
|---|---|
| መክሥት | መግለጫ |

በግዕዝ ቋንቋ አንድን ቃል ከሌላ ቃል ጋር ለማናበብ ሦስት መንገዶች አሉ ።
፩ኛ—የቃሉን(የስሙን መድረሻ ፊደል በመለወጥከሌላ ውቃል ጋርእናናብባለን ።
በመጀመሪያ መድረሻቸው ሣልስ የሆነ ስሞችን እንዴት እንደሚናበቡ እንመለከታለን ።

ቃላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዜናዊ | ነጋሪ | ሐዳፊ | ሾፌር ( አንቀሳቃሽ |
| መራሂ | መሪ | መዋኢ | አሸናፊ |
| ቀታሊ | ገዳይ | ነባቢ | ተናጋሪ |
| ኖላዊ | ጠባቂ (እረኛ) | ዘራዊ | በታኝ |
| ሐራሲ | ገበሬ (አራሽ) | ፈናዊ | ላኪ |
| ሰማኢ | ሰሚ | ጸራቢ | ጠራቢ |
| ጸሐፊ | ጣፊ | ገዛሚ | ቆራጭ |

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው መጨረሻቸው ሳልስ የሆኑ ቃላት ከሌላ ቃል ጋር ሲናበቡ ሣልስ የነበረው መድረሻቸው ወደሐምስ ይለወጣል ።
ይህንንም ቀጥሎ እንማራለን ።

| | |
|---|---|
| ዜናዌ ዜና | ወሬ ነጋሪ (ወሬ አንባቢ) |
| መራሄ መንግሥት | የመንግሥት መሪ |
| ቀታሌ አንበሳ | አንበሳ ገዳይ |
| ኖላዌ አባግዕ | የበግ እረኛ ( ጠባቂ) |
| ሐራሴ ምድር | መሬት አራሽ (የምድር አራሽ ) |
| ሰማኤ ነገር | ነገር ሰሚ |
| ጸሐፌ መልእክት | መልእክት ጸሐፊ |
| ሐዳፌ ሐመር | መርከብ ነጂ |
| መዋኤ ፀር | የጠላት አሸናፊ |
| ነባቤ ኅቡዓት | ምሥጢር ተናጋሪ |
| ዘራዌ ንዋይ | ገንዘብ በታኝ |
| ፈናዌ መልእክት | ደብዳቤ ላኪ |
| ጸራቤ ዕብን | ድንጋይ ጠራቢ |
| ገዛሜ ዖም | ዛፍ ቆራጭ |

ከዚህ በላይ አንዱን ቃል ከሌላው ቃል ጋር በማናበብ በተመለከትናቸው ቃላት ባጭሩ እንደሚከተለው ዐረፍተ ነገር እንሠራለን ።

| | ዐረፍተ ነገር |
|---|---|
| ክቡር ውእቱ ሐራሴ ምድር | የመሬት አራሽ ክቡር ነው |
| አነ ውእቱ ኖላዌ አባግዕ | የበጎች ጠባቂ እኔ ነኝ |
| መጽአ ሐዳፌ ሐመር | መርከብ ነጂው መጣ |
| ዝንቱ ብእሲ ኮነ መዋኤ ጸር | ይህ ሰው ጠላትን አቸናፊ (አሸናፊ ሆነ |
| ስኩር ውእቱ ዘራዌ ንዋይ | ገንዘብ በታኝ ሰካራም ነው |
| ቀርበ ኀበ ሰብእ ነባቤ ኅቡዓት | ምሥጢር ተናጋሪው ወደ ሰዎች ቀረበ |
| ተእኀዘ ቀታሌ አንበሳ | አንበሳ ገዳዩ ተያዘ |
| ሳሙኤል ውእቱ ጸራቤ ዕብን | ሳሙኤል ድንጋይ ጠራቢ ነው ። |



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org